## ማውጫ ገጽ


መቅድም ........ 2

ምዕራፍ ፩

መሠረተ ግእዝ ........ 3

፩,፩ ግእዝ የሚለው ቃል ትርጓሜ........3

፩,፪ ፊደላተ ግእዝ ........3

፩,፫ አኀዝ........ 4

፩.፬ መራሕያን........ 5

፩.፭ የግስ ዝርዝር በመራሕያን(የባለቤት ዝርዝር)........7

፩.፮ የስም ዝርዝር በመራሕያን ........ 9

፩.፯ መስተዋድዳን ቀለማት ........ 11

፩.፰ የቃላት ጥናት........15

ምዕራፍ ፪

ሥርዓተ ንባብ ዘልሣነ ግእዝ........18

፪.፩ የንባብ ዓይነቶች........18

፪.፪ ተናባቢ ንባብ........19

፪.፫ የተጸውዖ ስሞች የንባብ ሕግጋት ........20

፪.፬ የሆሄያት ተጽእኖ........ 21

፪.፭ መጠይቃን ቃላት ........23

፪.፮ የቃላት ጥናት ........25

ምዕራፍ ፫

ግሥ........27

፫.፩ የግሥ ስልት ........27

፫.፪ መራኁት(የግሥ መነሻዎች) ........28

፫.፫ አርእስት ግሥ ........28

፫.፬ ሠራዊት ግሥ ........29

፫.፭ የአርእስተ ግሥ ገሢሦት (የግሥ መሪዎች እርባታ)........32

፫.፮ ጸዋትው የግሥ እርባታ ሕግጋት........33

፫.፯ ንዑስ (መለስተኛ) እርባታ........37

፫.፰ ዝርዝር እርባታ........39

፫.፱ የግሥ ጥናት........47

# መቅድም

ሕዝብ ባለበት ቋንቋ አለ። ቋንቋ ካለ ሕዝብ አለ። ያለ ቋንቋ የሚኖር ሕዝብ የለም። ያለ ሕዝብም የሚነገር ቋንቋ የለም።ቋንቋ የሕዝብ አኗኗርና እድገት መፍቻ ቁልፍ ነውና። ሕዝብም የቋንቋ እድገት መመላለሻ በር ነውና። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢትዮጵያ መኖር ከጀመረበት ዘመን ጀምሮ የራሱ ሀገራዊ ቋንቋ ነበረው፤ አለውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ነባር ሕዝብ ለመሆኑ በዓለም ታሪክ ከሚታወቅባቸው ነባር ታሪኮቹ ዋናውና አንደኛው ቋንቋው ነው።

በዓለም ላይ ካሉ የራሳቸው ፊደልና አኀዝ ካላቸው በጣም ጥቂት ቋንቋዎች ውስጥ አንዱ ግእዝ ነው። በተለይም በአፍሪካ ክፍለ ዓለም ካሉት ሀገራት ኢትዮጵያ ብቸኛዋ የራሷ ፊደልና አኃዝ ያለው ቋንቋ ያላት ሀገር አድርጓታል። የግእዝ ቋንቋ ከድንጋይ ዘመን እስከ ብራና ዘመን፤ ከብራና ዘምን እስከ ወረቀት ዘመን በጽሑፍ ቋንቋነት ሲያገለግል የኖረ ቋንቋ ነው። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም የኢትዮጵያን ባህልና ታሪክ ከትባ ያቆየችው በዚሁ ቋንቋ ነው። ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንና የኢትዮጵያ ታሪክ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።

ግእዝ ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ግእዝ ፊደል ግእዝ ድምጽ ብቻ ነበረው። ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያሉት ድምጾች የተጨመሩት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ዘመን ነው። አቡነ ሰላማ (አባ ፍሬምናጦስ) ለኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ ከተሾመ በኋላ የክርስትና ትምህርትን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ቅዱሳት መጽሐፍትን ከውጭ ቋንቋ ወደ ግእዝ ለመተርጎም በሚያመች መንገድ ግእዝ ብቻ የነበረው ፊደለ ግእዝ (ድምጽ) እስከ ሳብዕ እንዲሆን አድርገውታል። ከዚህ በተጨማሪ በ«አበገደ» ይጻፍ የነበረው የፊደላት ቅደም ተከተል በ«ሀለሐመ» እንዲሆን አድርገዋል።

አሁን ባለው ሁኔታ ግእዝ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ባይሆንም የማኅሌትና የሥነ- ጽሑፍ ቋንቋ ሆኖ ከማገልገሉም በላይ በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች በመሰጠት ላይ ነው። ግእዝ ለሌሎች ቋንቋዎች በተለይም ለአማርኛና ለትግረኛ ቃላትን በማዋስና ሥነ- ጽሑፍን በማበርከት የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ አስችሏቸዋል። ቋንቋው በታሪካዊቷ ሀገር በኢትዮጵያ የሥራና የሥነ- ጽሑፍ ቋንቋ ሆኖ ለብዙ ሺህ ዘመናት የቆየ ከመሆኑ የተነሳ ለታሪክ አጥኝዎች ከፍተኛ ጥቅም አለው።

## የግእዝ ቋንቋ መለያ ባህርያት

- ♣ ጥንታዊና ታሪካዊ ነው።
- ♣ የራሱ የሆነ ሥርዓተ ጽሕፈትና ሥርዓተ ንባብ አለው።
- ♣ የራሱ መቁጠሪያ ቁጥር (አኀዝ) አለው።

## የትምህርቱ ዓላማ

- ⌖ የግቢ ጉባዔ ተማሪዎች የቋንቋውን ታላቅነትና ጠቀሜታ ማሳወቅ።
- ⌖ በግእዝ ቋንቋ የተጻፉትን የታሪክ፣ የሃይማኖት፣ የጥበብ እና የፍልስፍና መጻሕፍትን ማንበብና እና መመርመር እንዲችሉ ማድረግ።
- ⌖ ተዳክሞ የነበረውን የግእዝ ቋንቋ ትምህርት ማሳደግ።
- ⌖ ቅኔ ለሚማሩ ተማሪዎች ስለቋንቋው ሰዋስው ማሳወቅ።
- ⌖ አጫጭር ንግግሮችን ፤ መነባንቦችን፤ ጭውውቶችን በግእዝ እንዲጽፉና እንዲያቀርቡ ማስቻል።

## የትምህርቱ ይዘት

ይህ የግእዝ መማሪያ ጽሑፍ የተዘጋጀው መሰረታዊውን የግእዝ ቋንቋ ሰዋስው በአጭር ጊዜ ለተማሪዎች ለማስጨበጥ እንዲቻል ተደርጎ ነው።ጽሑፉ ለአንደኛ ዓመት እና ለሁለተኛ ዓመት ተብሎ ለሁለት የተከፈለ ነው። እያንዳንዳቸው ክፍሎች ሶስት ሶስት ምዕራፍ እንዲኖራቸው ተደርገው ተዘጋጅተዋል። በእያንዳንዱ ምዕራፍም ከሰዋስው ባለፈ የንግግር ክሂሎትን ለማዳበር እንዲረዱ በማሰብ የቃላት ጥናትና ንባበ ልሣነ ግእዝ ተካተውባቸዋል። ባጭሩ ይህ ጽሑፍ የተዘጋጀው ሰፊውን የግእዝ ቋንቋ ሰዋስው በቀላል ዘዴ እና ባጭር ጊዜ ለማስረዳት በማሰብ ነው።

# ምዕራፍ ፩

# መሠረተ ግእዝ

## ፩.፩ ግእዝ የሚለው ቃል ትርጓሜ

1, <u>የፊደል ስም ሲሆን</u>፡- ግእዝ የሚለው ቃል የፊደል ስም ሲሆን የመጀመሪያ፣ ፈርጅና ቅጥያ የሌለው፣ከዘመነ አብርሃ ወአጽብሐ በፊት የነበረው የመጀመሪያ ፊደል ማለት ነው።

‘ሀ’- ግእዝ፣ ‘ሁ’- ካዕብ፣ ‘ሂ’- ሣልስ፣ ወዘተ... ስንል ‘ሀ’- አንደኛ፣ ‘ሁ’- ሁለተኛ፣ ‘ሂ’- ሦስተኛ ወዘተ… ማለታችን ነው።

2, <u>የንባብ ስም ሲሆን</u>፡- ግእዝ የሚለው ቃል የንባብ ስም ሲሆን የመጀመሪያ ንባብ፣ ውርድ ንባብና ቁም ንባብ ከሚባሉት ውስጥ የመጀመሪያው ማለት ነው። በአብነት ትምህርት ቤቶች በመጀመሪያ የሚነበበው ግእዝ ንባብ ነው። ከዚያ ውርድ ንባብ ከዚያም ቁም ንባብ ይከተላል።

3, <u>የዜማ ስም ሲሆን</u>፡- የቅዱስ ያሬድ የዜማ ስልቶች ሦስት ሲሆኑ አነርሱም ግእዝ፣ ዕዝልና አራራይ ናቸው። ስለዚህ ግእዝ የዜማ ስልት ይሆናል ማለት ነው።

4, <u>የቋንቋ ስም ሲሆን</u>፡- የመጀመሪያ ቋንቋ፣ አዳማዊ ቋንቋ፣ ሴማዊ ቋንቋ፣ ጥንታዊ ቋንቋ ማለት ነው።

## ፩.፪ ፊደላተ ግእዝ

የግእዝ ቋንቋ ፊደላት ጠቅላላ ብዛት ሠላሳ ሲሆን ሃያ ስድስቱ መደበኛና አራቱ ዲቃላ ፊደላት ናቸው። በአማርኛ ቋንቋ ከሚታወቁት ሠላሳ ሦስት መደበኛ ፊደላት ውስጥ ሰባቱ በግእዝ ያልነበሩ እና በአማርኛ የተጨመሩ ናቸው። እነዚህም በፊት ከነበሩት የግእዝ ፊደላት ትንሽ ለውጥ በማድረግ የተገኙ ናቸው። እነርሱም ከታች የተጠቀሱት ናቸው።

| | |
|---|---|
| ሸ-- ‘ሰ’ ን | ጨ-- ‘ጠ’ ን |
| ኘ-- ‘ነ’ ን | ዠ-- ‘ዘ’ ን |
| ጀ-- ‘ደ’ ን | ኸ-- ‘ከ’ ን በተወሰነ ቅርጽ በመቀየር የተገኙ ናቸው። |
| ቸ-- ‘ተ’ ን | |

ከነዚህ የተረፉት ሃያ ስድስቱ መደበኛ ፊደላት የግእዝ ፊደላት ናቸው።

በግእዝ ቋንቋ ዲቃላ ፊደላት የሚባሉት ከመደበኛ ፊደላት የተገኙ ሲሆኑ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኰ | ኵ | ኲ | ኳ | ኴ |
| ጐ | ጕ | ጒ | ጓ | ጔ |
| ኈ | ኍ | ኊ | ኋ | ኌ |
| ቈ | ቍ | ቊ | ቋ | ቌ |

**ሞክሸ ፊደላት**

ሞክሸ ፊደላት የሚባሉት አንድ ዓይነት ድምፅት ያላቸው ሆነው የተለያየ ቅርፀ ፊደል ያላቸው ናቸው። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ፣ ሐ፣ ኀ፤ አ፣ ዐ፤ ጸ፣ ፀ፤ ሰ፣ሠ

እነዚህም ፊደላት አንደኛው ከአንደኛው ተለይቶ የሚታወቅበት ስም ተሰጥቶታል።

ሀ-- ሃሌታው ‘ሀ’ ይባላል። ሃሌ ሉያ ለአብ ብለን ስንጽፍ የምንጠቀመው ይህን ፊደል ስለሆነ ነው።

ሐ-- ሐመሩ ‘ሐ’ ይባላል። ሐመር ብለን ስንጽፍ የምንጠቀመው ይህን ፊደል ስለሆነ ነው።

ኀ-- ብዙኀኑ ‘ኀ’ ይባላል። ብዙኀ ብለን ስንጽፍ የምንጠቀመው ይህን ስለሆነ ነው።

አ-- አልፋው ‘አ’ ይባላል። አልፋ ወዖሜጋ ብለን ስንጽፍ የምንጠቀመው ይህን ስለሆነ ነው።

ዐ-- ዓይኑ ‘ዐ’ ይባላል። ዓይን ብለን ስንጽፍ የምንጠቀመው ይህን ስለሆነ ነው።

ጸ-- ጸሎቱ ‘ጸ’ ይባላል። ጸሎት ብለን ስንጽፍ የምንጠቀመው ይህን ስለሆነ ነው።

ፀ-- ፀሐዩ ‘ፀ’ ይባላል። ፀሐይ ብለን ስንጽፍ የምንጠቀመው ይህን ስለሆነ ነው።

ሠ-- ንጉሡ ‘ሠ’ ይባላል። ንጉሥ ብለን ስንጽፍ የምንጠቀመው ይህን ስለሆነ ነው።

ሰ-- እሳቱ ‘ሰ’ ይባላል። እሳት ብለን ስንጽፍ የምንጠቀመው ይህን ስለሆነ ነው።

ስለዚህ ‘ሠ’ ን ‘ንጉሡ’ የሚል ሰው ‘ንጉሥ’ ብሎ ሲጽፍ ‘ንጉስ’ ብሎ ከጻፈ ታላቅ ስህተት ይሆንበታል።

እነዚህ ሞክሸ ፊደላት አንዱ በአንዱ ቦታ አይገቡም። ከገቡ ግን የትርጉም ለውጥ ሊያስከትሉ ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| ምሳሌ:- ሠረቀ-- ወጣ | አመት-- አገልጋይ |
| ሰረቀ-- ሰረቀ | ዓመት-- ዘመን |

ሰዐለ-- ስዕል ሳለ　　　　አ/አ-- አዲስ አበባ
ሰአለ-- ለመነ　　　　ዓ/ዓ-- ዓመተ ዓለም

**፩,፫ አኀዝ**

የግእዝ ቋንቋን በሥነ-ጽሑፍ ምሉዕ ካደረጉት ነገሮች አንዱ የራሱ የሆነ አኀዝ ያለው መሆኑ ነው። አኀዝ የሚለው ቃል አኀዘ-- ያዘ፣ ቆጠረ፣ ጀመረ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ቁጥር፣ መጀመሪያ፣ መያዣ ማለት ነው። አኀዝ ተብሎ በግእዙ 'ኀ' ሲጻፍ ነጠላ ቁጥርን ያመለክታል፤ አኃዝ ተብሎ በራብዑ 'ኃ' ሲጻፍ ብዙ ቁጥርን ያመለክታል። ይህም አኀዝ-- ቁጥር፤ አኃዝ-- ቁጥሮች ማለት ነው። የግእዝ አኀዝ መሥራች ቁጥሮች ብዛታቸው ሃያ ነው። በእነዚህ በሃያዎቹ ማንኛውንም ቁጥር መጻፍ ይቻላል። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

መዋቅር　　　　የግእዝ አኀዝ / በፊደል/ የዐረበኛ ቁጥር

| | | |
|---|---|---|
| ፩/ አሐዱ/1 | ፰/ስምንቱ/8 | ፷/ስድሳ/ስሳ/60 |
| ፪/ክልዔቱ/2 | ፱/ተስዐቱ/9 | ፸/ሰብዐ/70 |
| ፫/ሠለስቱ /3 | ፲/ዐሠርቱ/10/ | ፹/ሰማንያ/80 |
| ፬/አርባዕቱ /4 | ፳/እሥራ/20 | ፺/ተስዐ/90 |
| ፭/ኃምስቱ/5 | ፴/ሠላሳ/30 | ፻/ምዕት/100 |
| ፮/ስድስቱ /6 | ፵/አርብዓ/40 | ፼/እልፍ/10000 |
| ፯/ሰብዐቱ/7 | ፶/ሃምሳ/50 | ፻፼/አእላፋት/1000000 |

በግእዝ ቋንቋ ዜሮን የሚወክል አኀዝ የለም። ይህም የሆነው በግእዝ አሥርን ለመጻፍ ራሱን የቻለ አሥር ቁጥር ስላለ ነው። ከአንድ ጀምሮ እስከ ተፈለገው ቁጥር ድረስ ከላይ ያየናቸውን መሥራች ቁጥሮች በመጠቀም መጻፍ ይቻላል።

በግእዝ ቋንቋ አምስት የአኀዝ ዓይነቶች አሉ።እነርሱንም እንደሚከተለው እናያቸዋል።

፩, ሒጋዊ አኀዝ፡- ይህ የአኀዝ ዓይነት ከታወቀ ቁጥር ውስጥ ስንተኛነትን የሚነግረን ነው።

ምሳሌ፡- ኣሐድ/ቀዳማይ　　አንደኛ
ካልእ/ካልዐይ　　ሁለተኛ
ሣልስ/ሣልሳይ　　ሦስተኛ　ወዘተ

፪, ክፍላዊ አኀዝ፡- ይህ ደግሞ ከሙሉ ነገር ምን ያክል የሚለውን የሚያሳውቅ ነው።

ምሳሌ፡- ካልዒት　አንድ ሁለተኛ/ግማሽ
ሣልሲት　አንድ ሦስተኛ/ሲሶ
ራብዒት　አንድ አራተኛ/ሩብ　ወዘተ

፫, ዕፅፋዊ አኀዝ፡- እጥፍነትን ያሳውቀናል።

ምሳሌ፡- ካዕብተ ክልዔቱ　　ሁለት እጥፍ
ካዕብተ ሰለስቱ　　ሦስት እጥፍ
ካእብተ አርባዕቱ　　አራት እጥፍ　ወዘተ

፬, መድበላዊ አኀዝ፡- መድበላዊ የሚባለው በውል የማይታወቁ ቁጥሮችን የሚነግረን ነው። ይህም ማለት ጥቂትና ብዙ መሆኑን እንጅ ቁጥሩን በውል ለይተን አናውቀውም።

ብዙኅ　ብዙ
ንስቲት　ትንሽ
ኅዳጥ　ጥቂት

፭, መደባዊ አኀዝ፡- የቁጥሮችን ወይም ነገሮችን ብዛት ስንትነት በውል የሚያሳውቀን ሲሆን ከአንድ ይጀምራል።

፩　፪　፫　፬　፭　፮　፯　፰　፱　፲　፲፩　- - - - - - - - - -

**ቁጥሮችን መቀየር**

ከላይ ባየናቸው መደባዊ አኃዝ መሠረት ማንኛውንም የዐረበኛ ቁጥር ወደ ግእዝ መለወጥ እንችላልን። የግእዝ ቁጥርንም ወደ ዐረበኛ መለወጥ እንችላለን። የአረብኛ ቁጥሮችን ወደ ግእዝ ቁጥር ስንለውጥ ከቀኝ ወደ ግራ ሁለት ሁለት አድርገን ከከፋፈልን በኋላ ነው። ምሳሌ፡-«235637»ን ለመቀየር 23 56 37 ይህም 23 እልፍ 56 ምዕት እና 37 ይሆናል። በግእዝ ሲነበብም

እሥራ ወሰለስቱ እልፍ ሃምሳ ወስድስቱ ምዕት ሰላሳ ወሰብዐቱ ተብሎ ነው። ሲጻፍም ፳፫፼፶፮፻፴፯ ተብሎ ነው።

1. 2452 ሲቀየር ፳፬፻፶፪ ሲነበብም እሥራ ወአርባዕቱ ምዕት ሃምሳ ወክልዔቱ
2. 906 ሲቀየር ፱፻፮ ሲነበብም ተሰአቱ ምዕት ወስድስቱ
3. 1235272 ሲቀየር ፻፼፳፫፼፶፪፻፸፪ ሲነበብም አእላፋት እሥራ ወሰለስቱ እልፍ ሃምሳ ወክልዔቱ ምዕት ሰብዐ ወክልዔቱ
4. 74839200 ሲቀየር ፸፬፼፻፹፫፼፺፪፻ ሲነበብም ሰብዐ ወአርባዕቱ አእላፋት ሰማንያ ወሠለስቱ እልፍ ተስዐ ወክልዔቱ ምዕት

የግእዝን ቁጥር ወደ አረብኛ ለመለወጥ መጀመርያ የግእዙን ቁጥር መበተን ነው።
ምሳሌ፡-«፪፼፸፮፻»ን ለመቀየር 2x10000 ሲደመር 76x100 ማድረግ ነው።ይህም 20000+7600=27600 ይሆናል።

**ምልማድ ፩**

፩ ቁጥሮችን ቀይሩ በግእዝ መጠሪያ ስማቸውንም ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| 3652 | 400002 | 2000045 |
| 189 | 40002 | 102020 |
| 1794625 | 4002 | 220022 |
| 340201 | 402 | 100100 |

፪ ቁጥሮችን በግእዝ መጠሪያ ስማቸውን ከጻፋችሁ በኋላ ቀይሯቸው።

፶፮፼፸፻ ፳፻፸፳ ፺፼፻ ፪፼፳፫፻፹

**፩.፬ መራሕያን**

መራሕያን “መርሐ- መራ” ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም መሪዎች ማለት ነው፡፡ መራሕያን የሚባሉት በሰው ስም ፋንታ ተተክተው የሚነገሩ የእርባታ መደቦች ናቸው፡፡ መራሕያን የተጸውዖ (የመጠሪያ) ስሞች፣ የተቀብዖ ስሞች፣ የነገር፣ የአካልና የግብር ስሞች ሁሉ አጻፋ እየሆኑ የሚነገሩ የደቂቅ ሰዋስው ክፍሎች ናቸው፡፡ በአማርኛ ሰዋስው ተውላጠ ስሞች ይባላሉ፡፡ ብዛታቸው አሥር ሲሆን የሚከተከሉት ናቸው፡፡

| መራሒ | አማርኛ | መራሒ | አማርኛ |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | እሱ | አንትሙ | እናንተ(**ተ**) |
| ውእቶሙ | እነርሱ(**ተ**) | አንቲ | አንቺ |
| ይእቲ | እርሷ | አንትን | እናንተ(**አ**) |
| ውእቶን | እነርሱ(**አ**) | አነ | እኔ |
| አንተ | አንተ | ንሕነ | እኛ |

እነዚህም አሥሩ መራሕያን በቁጥር በፆታ እና በመደብ እንደሚከተለው ይከፋፈላሉ፡፡

ሀ, በአንድና በብዙ ቁጥር ሲከፈሉ

ነጠላ ቁጥር: ውእቱ፣ ይእቲ፣ አንተ፣ አንቲ፣ አነ

ብዙ ቁጥር: ውእቶሙ (እሙንቱ)፣ ውእቶን (እማንቱ) ፣አንትሙ፣ አንትን፣ ንሕነ

ለ, በተባዕታይና በአንስታይ ፆታ ሲከፈሉ

ተባዕታይ ፆታ፡- ውእቱ፣ ውእቶሙ፣ አንተ፣ አንትሙ

አንስታይ ፆታ፡- ይእቲ፣ ውእቶን፣ አንቲ፣ አንትን

- ከመራሕያን መካከል ፆታ የማይለዩት አነ እና ንሕነ ናቸው።

ሐ, በሩቅና ቅርብ መደብ ሲከፈሉ

በንግግር ጊዜ ፡-

- ተናጋሪው አንደኛ መደብ ይባላል።
- አድማጩ ሁለተኛ መደብ ይባላል።
- ተናጋሪ ያልሆኑ በማድመጥም በዋናነት የማይሳተፉ ስለእነርሱ ነገሩ የሚነገርላቸው ሦስተኛ መደቦች ይባላሉ።

<u>አንደኛ መደብ</u>፡- አነ፣ ንሕነ

<u>ሁለተኛ መደብ</u>፡- አንተ፣ አንትሙ፣ አንቲ፣ አንትን

<u>ሦስተኛ መደብ</u>፡- ውእቱ፣ ውእቶሙ፣ ይእቲ፣ ውእቶን

**የመራሕያን አገልግሎት**

መራሕያን በዐ/ነገር ውስጥ ሶስት ዓይነት አገልግሎት አለቸው፡፡ይህንንም ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን

፩ <u>የስም ምትክ ሆነው ያገለግላሉ</u>፡-

መራሕያን በዐ/ነገር ውስጥ ስምን ተክተው በባለቤትነት ይነገራሉ፡፡በዚህም አገልግሎታቸው ተውላጠ ስም ይባላሉ፡፡የሚነገራቸው ትርጉምም እንደሚከተለው ነው፡፡

| መራሒ | አማርኛ | መራሒ | አማርኛ |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | እሱ | አንትሙ | እናንተ(ተ) |
| ውእቶሙ | እነርሱ(ተ) | አንቲ | አንቺ |
| ይእቲ | እርሷ | አንትን | እናንተ(አ) |
| ውእቶን | እነርሱ**(አ)** | **አነ** | እኔ |
| አንተ | አንተ | **ንሕነ** | እኛ |

**ማስታወሻ፡-** መራሕያን የስም ምትክ ሆነው እንዲያገለግሉ ከግስ በፊት መምጣት አለባቸው፡፡

ምሳሌ፡- ንሕነ አንበብነ መዝሙረ ዳዊት

ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ወትፈደፍድ እምሱራፌል

አኮ አንትሙ ዘኀረይክሙኒ ወሤምክሙኒ አላ አነ ኀረይኩክሙ

ውእቱ ጸለየ በቤተ ክርስቲያን

፪ <u>ነባር አንቀጽ ሆነው ያገለግላሉ</u>፡-

መራሕያን በአረፍተ ነገር ውስጥ ዐ/ነገሩን በማሰር እንደ ማሰሪያ አንቀጽ ያገለግላሉ፡፡እንደ ዚህ ባለው አገልግሎታቸውም ነባር አንቀጽ ይባላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የሚኖራቸውም ትርጉም እንደሚከተለው ነው፡፡

| መራሒ | አማርኛ | መራሒ | አማርኛ |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ነው፣ ነበር፣ አለ | አንትሙ | ናችሁ፣ ነበራችሁ፣ አላችሁ |
| ውእቶሙ | ናቸው፣ ነበሩ፣ አሉ | አንቲ | ነሽ፣ ነበርሽ፣ አለሽ |
| ይእቲ | ናት፣ ነበረች፣ አለች | አንትን | ና ችሁ፣ ነበራችሁ፣ አላችሁ |
| ውእቶን | ናቸው፣ ነበሩ፣ አሉ | **አነ** | ነኝ፣ ነበሁ፣ አለሁ |
| አንተ | ነህ፣ ነበርህ፣ አለህ | **ንሕነ** | ነን፣ ~~ነበ ርሁ፣ አለሁ~~ |

መራሕያን ነባር አንቀጽ ሆነው እንዲያገለግሉ ከስም በኋላ ወይም ካሉት ክፍላተ ነገሮች በኋላ መምጣት አለባቸው። በዐ/ነገሩ ውስጥ ሌላ ማሰሪያ አንቀጽ ከሌለ ማሰሪያ አንቀጽ የሚሆኑት ነባር አንቀጾች ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-መኑ አነ

ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ

ማርያም ይእቲ ሙዳየ መና

ዛቲ ይእቲ ትእዛዝ እንቲአየ ከመ ትትፋቀሩ በበይናቲክሙ

አነ ውእቱ ሐረገ ወይን ዘፅድቅ ወአቡየ ተካሊሁ ውእቱ

፫ <u>አመልካች ቅጽል ሆነው ያገለግላሉ</u>፡-

መራሕያን በዐረፍተ ነገር ውስጥ አንድን ነገር ከጓደኞቹ ለይተን «ይህ» ወይም «ያ» ብለን ጠቁመን ለማመልከት ያገለግላሉ፡፡እንደዚህ ባለው አገልግሎታቸውም አመልካች ቅጽል ይባላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የሚኖራቸውም ትርጉም እንደሚከተለው ነው፡፡

| መራሒ | አማርኛ | መራሒ | አማርኛ |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ያ | አንትሙ | እናንተ(ተ) |
| ውእቶሙ | እነዚያ(ተ) | አንቲ | አንቺ |
| ይእቲ | ያች | አንትን | እናንተ(አ) |
| ውእቶን | እነዚያ**(አ)** | **አነ** | እኔ |
| አንተ | አንተ | **ንሕነ** | እኛ |

መራሕያን ~~ገባር አንቀጽ~~ ሆነው እንዲያገለግሉ ከስም በፊት መምጣት አለባቸው፡፡

ምሳሌ፦ውእቱ ወልድ ሖረ ኀበ ሀገረ እንግልጣር
ይእቲ ይእቲ ዘቀተለቶ ለከይሲ
ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ
አንትሙ አርድእት አንትሙ

- በንግግር ጊዜ በተሳቢነት የሚያገለግሉ የመራሕያን ክፍሎች ገቢር መራሕያን (ተሳቢ መራሕያን) ይባላሉ፡፡ እነዚህም፦

**ኪያሁ**= እሱን　**ኪያከ**= አንተን　**ኪያየ**= እኔን
**ኪያሆሙ**= እነርሱን　**ኪያክሙ**= እናንተን　**ኪያነ**= እኛን
**ኪያሃ**= እርሷን　**ኪያኪ**= አንችን
**ኪያሆን**= እነርሱን　**ኪያክን**= እናንተን

ምሳሌ፦ ኪያሁ አፈቅር
ኪያክሙ ኢያርእየኒ
ኪያከ እግዚኦ ንሴብሐከ

- በንግግር ጊዜ በባለቤትነት የሚያገለግሉ የመራሕያን ክፍሎች ድርብ መራሕያን ይባላሉ፡፡ እነዚህም፦

**ለሊሁ**= ራሱ　**ለሊከ**= ራስህ　**ለልየ**= ራሴ
**ለሊሆሙ** = ራሳቸው　**ለሊክሙ**= ራሳችሁ　**ለሊነ**= ራሳችን
**ለሊሃ**= ራሷ　**ለሊኪ**= ራስሽ
**ለሊሆን**= ራሳቸው　**ለሊክን**= ራሳችሁ

ምሳሌ፦ለልየ ውእቱ ዘገበርኩ ዘንተ ግብረ
ለሊነ ነአምር ኵሎ ዘኮነ
ወለልየ ርኢኩ ወአነ ሰማዕቱ ከመ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለእግዚአብሔር

## ፩.፫ የግስ ዝርዝር በመራሕያን(የባለቤት ዝርዝር)

በመራሕያን ባለቤትነት ግሶች መጠነኛ ለውጦችን እያደረጉ የሚዘረዘሩት መዘርዘር የባለቤት ዝርዝር ይባላል። ለባለቤት ዝርዝር የሚረዱ ቀለማት መዘርዝራን ተውላጠ ስም ይባላሉ። እነርሱም ከግሱ መጨረሻ የሚገቡ ባዕዳን ቀለማት ናቸው። የግሶችም አዘራዘር የሚከተለውን ይመስላል።

ሀ , በውእቱ ጊዜ የሚጨመርም ሆነ የሚቀየር የለም ግስ የሚገኘው በውእቱ ባለቤትነት ስለሆነ
ለ , በውእቶሙ ጊዜ የግሱን መድረሻ ቀለም ወደ ካዕብ መቀየር ብቻ ነው፡፡
ሐ , በይእቲ ጊዜ የግሱ መድረሻ ፊደል ሳይቀየር “ት” ፊደልን መጨመር ነው፡፡
መ , በውእቶን ጊዜ የግሱን መድረሻ ፊደል ወደ ራብዕ መቀየር ነው፡፡
ሠ , በአንተ ጊዜ የግሱን መድረሻ ፊደል ወደ ሳድስ ከቀየርን በኋላ “ከ” ፊደልን መጨመር ነው፡፡
ረ , በአንቲ ጊዜ የግሱን መድረሻ ፊደል ወደ ሳድስ ከቀየርን በኋላ “ኪ” ፊደልን መጨመር ነው፡፡
ሰ , በአንትሙ ጊዜየግሱን መድረሻ ፊደል ወደ ሳድስ ከቀየርን በኋላ “ክሙ” ፊደልን መጨመር ነው፡፡
ሸ , በአንትን ጊዜ የግሱን መድረሻ ፊደል ወደ ሳድስ ከቀየርን በኋላ “ክን” ፊደልን መጨመር ነው፡፡
ቀ , በአነ ጊዜ የግሱን መድረሻ ፊደል ወደ ሳድስ ከቀየርን በኋላ “ኩ” ፊደልን መጨመር ነው፡፡
በ , በንሕነ ጊዜ የግሱን መድረሻ ፊደል ወደ ሳድስ ከቀየርን በኋላ “ነ” ፊደልን መጨመር ነው፡፡

- የተለየ ህግ የሌላቸው ግሶች ሁሉ ከላይ ባየነው አረባብ መሰረት ይዘረዘራሉ፡፡

ምሳሌ ፡-

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ፡ቀተለ | ዘገበ | ሐወጸ | ዐቀበ | መጽወተ | ሰከበ |
| ውእቶሙ | ፡ቀተሉ | ዘገቡ | ሐወጹ | ዐቀቡ | መጽወቱ | ሰከቡ |
| ውእቶን | ፡ቀተላ | ዘገባ | ሐወጻ | ዐቀባ | መጽወታ | ሰከባ |
| ይእቲ | ፡ቀተለት | ዘገበት | ሐወጸት | ዐቀበት | መጽወተት | ሰከበት |
| አንተ | ፡ቀተልከ | ዘገብከ | ሐወጽከ | ዐቀብከ | መጽወትከ | ሰከብከ |
| አንትሙ | ፡ቀተልክሙ | ዘገብክሙ | ሐወጽክሙ | ዐቀብክሙ | መጽወትክሙ | ሰከብክሙ |
| አንቲ | ፡ቀተልኪ | ዘገብኪ | ሐወጽኪ | ዐቀብኪ | መጽወትኪ | ሰከብኪ |
| አንትን | ፡ቀተልክን | ዘገብክን | ሐወጽክን | ዐቀብክን | መጽወትክን | ሰከብክን |
| አነ | ፡ቀተልኩ | ዘገብኩ | ሐወጽኩ | ዐቀብኩ | መጽወትኩ | ሰከብኩ |
| ንሕነ | ፡ቀተልነ | ዘገብነ | ሐወጽነ | ዐቀብነ | መጽወትነ | ሰከብነ |

**ማስታወሻ** ፡-፩ በባለቤት ዝርዝር(በግስ ዝርዝር) ጊዜ ወድቆ የሚነበበው ~~ይ~~አንትን ዝርዝር ብቻ ነው፡፡

ቀተልክን ዘገብክን ሰከብክን ዐቀብክን መጽወትክን ሰበክን (ሁሉም ወድቀው ይነበባሉ፡፡)

፪ በገብረ ቤቶች ዝርዝር በሁለተኛ እና በአንደኛ መደብ ሳድስ ቀለሙ ወደ ግእዝ ቀለም ተለውጦ ይዘረዘራል፡፡

ምሳሌ ፡-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ፡ ገብረ | መስወ | ከብደ | ለብሰ | ሠምረ |
| ውእቶሙ | ፡ ገብሩ | መስዉ | ከብዱ | ለብሱ | ሠምሩ |
| ውእቶን | ፡ ገብራ | መስዋ | ከብዳ | ለብሳ | ሠምራ |
| ይእቲ | ፡ ገብረት | መስወት | ከብደት | ለብሰት | ሠምረት |
| አንተ | ፡ ገበርከ | መሰውከ | ከበድከ | ለበስከ | ሠመርከ |
| አንትሙ | ፡ ገበ ርክሙ | መሰውክሙ | ከበድክሙ | ለበስክሙ | ሠመርክሙ |
| አንቲ | ፡ ገበርኪ | መሰውኪ | ከበድኪ | ለበስኪ | ሠመርኪ |
| አንትን | ፡ ገበርክን | መሰውክን | ከበድክን | ለበስክን | ሠመርክን |
| አነ | ፡ ገበርኩ | መሰውኩ | ከበድኩ | ለበስኩ | ሠመርኩ |
| ንሕነ | ፡ ገበርነ | መሰውነ | ከበድነ | ለበስነ | ሠመርነ |

፫, በ"ሀ" እና በ"አ" የሚጨርሱ ግሶ ች ሲዘረዘሩ በአንደኛ እና በሁለተኛ መደብ ቅድመ መድረሻቸውን ወደ ራብዕ ይለውጣሉ፡፡

ምሳሌ ፡-

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ፡ ባልሓ | በልዐ | ጠፍሐ | ረብሐ | አምኀ | ፈትሐ |
| ውእቶሙ | ፡ ባልሑ | በልዑ | ጠፍሑ | ረብሑ | አምኁ | ፈትሑ |
| ውእቶን | ፡ ባልሓ | በልዓ | ጠፍሓ | ረብሓ | አምኃ | ፈትሓ |
| ይእቲ | ፡ ባልሓት | በልዐት | ጠፍሐት | ረብሐት | አምኀት | ፈትሐት |
| አንተ | ፡ ባላሕከ | በላዕከ | ጠፋሕከ | ረባሕከ | አማኅከ | ፈታሕከ |
| አንትሙ | ፡ ባላሕክሙ | በላዕክሙ | ጠፋሕክሙ | ረባሕክሙ | አማኅክሙ | ፈታሕክሙ |
| አንቲ | ፡ ባላሕኪ | በላዕኪ | ጠፋሕኪ | ረባሕኪ | አማኅኪ | ፈታሕኪ |
| አንትን | ፡ ባላሕክን | በላዕክን | ጠፋሕክን | ረባሕክን | አማኅክን | ፈታሕክን |
| አነ | ፡ ባላሕኩ | በላዕኩ | ጠፋሕኩ | ረባሕኩ | አማኅኩ | ፈታሕኩ |
| ንሕነ | ፡ ባላሕነ | በላዕነ | ጠፋሕነ | ረባሕነ | አማኅነ | ፈታሕነ |

፬, የ"ሀ" እና የ"አ" አመል ሁለት ቀለማት ብቻ ባላቸው ግሶች አይታይም፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ፡ ሦዐ | ቦአ | ቴሐ | ሎሀ | ጼሐ |
| ውእቶሙ | ፡ሦዑ | ቦኡ | ቴሑ | ሎሁ | ጼሑ |
| ውእቶን | ፡ሦዓ | ቦኣ | ቴሓ | ሎሃ | ጼሓ |
| ይእቲ | ፡ሦዐት | ቦአት | ቴሐት | ሎሀት | ጼሐት |
| አንተ | ፡ሦዕከ | ቦእከ | ቴሕከ | ሎህከ | ጼሕከ |
| አንትሙ | ፡ሦዕክሙ | ቦእክሙ | ቴሕክሙ | ሎህክሙ | ጼሕክሙ |
| አንቲ | ፡ሦዕኪ | ቦእኪ | ቴሕኪ | ሎህኪ | ጼሕኪ |
| አንትን | ፡ሦዕክን | ቦእክን | ቴሕክን | ሎህክን | ጼሕክን |
| ንሕነ | ፡ሦዕነ | ቦእነ | ቴሕነ | ሎህነ | ጼሕነ |
| አነ | ፡ሦዕኩ | ቦእኩ | ቴሕኩ | ሎህኩ | ጼሕኩ |

፫ "ቀ፡ከ፡ገ" በግስ መድረሻ ላይ ሲገኙ በሁለተኛ መደቦች እና በአንደኛ መደብ "በአነ" ጊዜ አመልካቹን "ከ" ን አስወጥተው ጠብቀው ይነበባሉ፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ምሳሌ ፡- | ውእቱ | ፡ ሰጠቀ | ኀደገ | ሰበከ | ወረቀ | መጠቀ |
| | ውእቶሙ | ፡ ሰጠቁ | ኀደጉ | ሰበኩ | ወረቁ | መጠቁ |
| | ውእቶን | ፡ ሰጠቃ | ኀደጋ | ሰበካ | ወረቃ | መጠቃ |
| | ይእቲ | ፡ ሰጠቀት | ኀደገት | ሰበከት | ወረቀት | መጠቀት |
| | አንተ | ፡ ሰጠቀ(ፐ) | ኀደገ(ፐ) | ሰበከ(ፐ) | ወረቀ(ፐ) | መጠቀ(ፐ) |
| | አንቲ | ፡ ሰጠቂ(ፐ) | ኀደጊ(ፐ) | ሰበኪ(ፐ) | ወረቂ(ፐ) | መጠቂ(ፐ) |
| | አንትን | ፡ ሰጠቅ(ፐ)ን | ኀደግ(ፐ)ን | ሰበክ(ፐ)ን | ወረቅ(ፐ)ን | መጠቅ(ፐ) ን |
| | አንትሙ | ፡ ሰጠቅ(ፐ)ሙ | ኀደግ(ፐ)ሙ | ሰበክ(ፐ)ሙ | ወረቅ(ፐ)ሙ | መጠቅ(ፐ)ሙ |
| | አነ | ፡ ሰጠቁ(ፐ) | ኀደጉ(ፐ) | ሰበኩ(ፐ) | ወረቁ(ፐ) | መጠቁ(ፐ) |
| | ንሕነ | ፡ ሰጠቅነ | ኀደግነ | ሰበክነ | ወረቅነ | መጠቅነ |

፬ "ነ" በግስ መድረሻ ላይ ሲገኝ በንሕነ ጊዜ ብቻ ባልንጀራውን "ነ"ን ውጦ ጠብቆ ይነበባል፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ፡ ወጠነ | በየነ | ማሰነ | አድነነ | መነነ | ኰነነ |
| ውእቶሙ | ፡ ወጠኑ | በየኑ | ማሰኑ | አድነኑ | መነኑ | ኰነኑ |
| ውእቶን | ፡ ወጠና | በየና | ማሰና | አድነና | መነና | ኰነና |
| ይእቲ | ፡ ወጠነት | በየነት | ማሰነት | አድነነት | መነነት | ኰነነት |
| አንተ | ፡ ወጠንከ | በየንከ | ማሰንከ | አድነንከ | መነንከ | ኰነንከ |
| አንትሙ | ፡ ወጠንክሙ | በየንክሙ | ማሰንክሙ | አድነንክሙ | መነንክሙ | ኰነንክሙ |
| አንቲ | ፡ ወጠንኪ | በየንኪ | ማሰንኪ | አድነንኪ | መነንኪ | ኰነንኪ |
| አንትን | ፡ ወጠንክን | በየንክን | ማሰንክን | አድነንክን | መነንክን | ኰነንክን |
| አነ | ፡ ወጠንኩ | በየንኩ | ማሰንኩ | አድነንኩ | መነንኩ | ኰነንኩ |
| ንሕነ | ፡ ወጠነ(ፐ) | በየነ(ፐ) | ማሰነ(ፐ) | አድነነ(ፐ) | መነነ(ፐ) | ኰነነ(ፐ) |

፭ በብህለ ቤቶች "የ" በስተመጨረሻ ሲገኝ በሁለተኛ እና በአንደኛ መደብ ቅድመ መድረሻውን ሳልስ አድርጎ ራሱን ይጎርድና በመዘርዝራን ተውላጠ ስም ይዘረዘራሉ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ምሳሌ ፡- | ውእቱ | ፡ ርእየ | ውእየ | ጥዕየ | ልህየ |
| | ውእቶሙ | ፡ ርእዩ | ውእዩ | ጥዕዩ | ልህዩ |
| | ውእቶን | ፡ ርእያ | ውእያ | ጥዕያ | ልህያ |
| | ይእቲ | ፡ ርእየት | ውእየት | ጥዕየት | ልህየት |
| | አንተ | ፡ ርኢከ | ውኢከ | ጥዒከ | ልሂከ |
| | አንትሙ | ፡ ርኢክሙ | ውኢክሙ | ጥዒክሙ | ልሂክሙ |
| | አንቲ | ፡ ርኢኪ | ውኢኪ | ጥዒኪ | ልሂኪ |
| | አንትን | ፡ ርኢክን | ውኢክን | ጥዒክን | ልሂክን |
| | አነ | ፡ ርኢኩ | ውኢኩ | ጥዒኩ | ልሂኩ |
| | ንሕነ | ፡ ርኢነ | ውኢነ | ጥዒነ | ልሂነ |

ምልማድ ፪

የሚከተሉትን ግሶች በአሥሩ መራሕያን ዘርዝሩ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ , ሰትየ | ሠ , ኀረየ | ቀ , ሀከከ | ነ , ንዕደ |
| ለ , ተፈሥሐ | ረ , ዘርከየ | በ , ተክህነ | ኘ , ፈልሰፈ |
| ሐ , ዘመወ | ሰ , ጻመወ | ተ , ሐበነ | አ , ከብረ |
| መ , ወርዘወ | ሸ , ኖፈቀ | ቸ , አስተብረከ | ወ , ብዕለ |

## ፩.፪ የስም ዝርዝር በመራሕያን

ግሦች በአሥሩ መራሕያን እንዴት እንደሚዘረዘሩ ባለፈው ክፍል አይተናል። ከግሥ ውጪ ያሉ ቃላትን (ስሞችን፣ ቅጽሎችን፣ አርእስትን፣ ዘርን) እንዴት እንደምንዘረዝር ደግሞ ከዚህ በታች እናያለን። በስም ዝርዝር ጊዜ ለስም ዝርዝር የሚረዱ በመጨረሻ የሚጨመሩ ቀለማት አገናዛቢ ቅጽል ይባላሉ። ስሞችን ስንዘረዝር በሦስት ከፍለን እናያቸዋለን።

1, በሳድስ የሚጨርሱ ነጠላ ስሞች እንደሚከተለው ይረባሉ።

ሀ, በውእቱ ጊዜ የሚጨመር ፊደል የለም። መድረሻ ቀለሙን ወደ ካዕብ መለወጥ ነው።

ለ, በውእቶሙ ጊዜ መድረሻውን ሳብዕ አድርጎ ‘ሙ’ ን መጨመር ነው።

ሐ, በይእቲ ጊዜ የሚጨመር ፊደል የለም። መድረሻ ቀለሙን ወደ ራብዕ መለወጥ ነው።

መ, በውእቶን መድረሻውን ሳብዕ አድርጎ ‘ን’ ን መጨመር ነው።

ሠ, በአንተ ጊዜ ‘ከ’ ፊደልን መጨመር ብቻ ነው።

ረ, በአንትሙ ጊዜ ‘ ክሙ’ ቀለምን መጨመር ብቻ ነው።

ሰ, በአንቲ ጊዜ ‘ ኪ’ ፊደልን መጨመር ብቻ ነው።

ቀ, በአንትን ጊዜ ‘ ክን’ ቀለምን መጨመር ብቻ ነው።

በ, በአነ ጊዜ ‘ የ’ ፊደልን መጨመር ብቻ ነው።

ተ, በንሕነ ጊዜ ‘ ነ’ ፊደልን መጨመር ብቻ ነው።

ምሳሌ፡-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| መራሒ | መንበር | ልብ | | | |
| ውእቱ | መንበሩ | ልቡ | | | |
| ውእቶሙ | መንበሮሙ | ልቦሙ | | | |
| ይእቲ | መንበራ | ልባ | | | |
| ውእቶን | መንበሮን | ልቦን | | | |
| አንተ | መንበርከ | ልብከ | | | |
| አንትሙ | መንበርክሙ | ልብክሙ | | | |
| አንቲ | መንበርኪ | ልብኪ | | | |
| አንትን | መንበርክን | ልብክን | | | |
| አነ | መንበርየ | ልብየ | | | |
| ንሕነ | መንበርነ | ልብነ | | | |

- በስም ዝርዝር ጊዜ ወድቆ የሚነበበው የውእቱ፣ ይእቲና ውእቶን እርባታ ብቻ ነው።

2, ከሳድስ ውጭ የሚጨርሱ ነጠላ ስሞች በሚዘረዘሩ ጊዜ ከላይ ካየናቸው የሚለዩት በሦስተኛ መደቦች ዝርዝር ጊዜ ነው።

ሀ, በውእቱ ጊዜ ምንም ሳይቀይሩ ‘ሁ’ ፊደልን መጨመር ነው።

ለ, በውእቶሙ ጊዜ ምንም ሳይቀይሩ ‘ሆሙ’ ፊደልን መጨመር ነው።

ሐ, በይእቲ ጊዜ ምንም ሳይቀይሩ ‘ሃ’ ፊደልን መጨመር ነው።

መ, በውእቶን ጊዜ ምንም ሳይቀይሩ ‘ሆን’ ፊደልን መጨመር ነው።

ምሳሌ፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| መራሒ | ሥጋ | ገቦ | አንበሳ |
| ውእቱ | ሥጋሁ | ገቦሁ | አንበሳሁ |
| ውእቶሙ | ሥጋሆሙ | ገቦሆሙ | አንበሳሆሙ |
| ይእቲ | ሥጋሃ | ገቦሃ | አንበሳሃ |
| ውእቶን | ሥጋሆን | ገቦሆን | አንበሳሆን |

3, ብዙ ስሞች/plular nouns/ ሲረቡ አብዛኞቹ መድረሻ ቀለማቸውን ሣልስ አድርገው (‘አንቲ’ ን እና ‘አነ’ ን ሳይጨምር) ባዕድ ቅጽል ይጨምራሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| መራሒ | ሐዋርያት | አብያት | ከናፍር |
| ውእቱ | ሐዋርያቲሁ | አብያቲሁ | ከናፍሪሁ |
| ውእቶሙ | ሐዋርያቲሆሙ | አብያቲሆሙ | ከናፍሪሆሙ |
| ይእቲ | ሐዋርያቲሃ | አብያቲሃ | ከናፍሪሃ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቶን | ሐዋርያቲሆን | አብያቲሆን | ከናፍሪሆን |
| አንተ | ሐዋርያቲከ | አብያቲከ | ከናፍሪከ |
| አንትሙ | ሐዋርያቲክሙ | አብያቲክሙ | ከናፍሪክሙ |
| አንቲ | ሐዋርያትኪ | አብያትኪ | ከናፍርኪ |
| አንትን | ሐዋርያቲክን | አብያቲክን | ከናፍሪክን |
| አነ | ሐዋርያትየ | አብያትየ | ከናፍርየ |
| ንሕነ | ሐዋርያቲነ | አብያቲነ | ከናፍሪነ |

5, ከላይ ከታዩት የስም እርባታ ስልቶች አፈንግጠው የሚረቡ ስሞች አሉ። እነዚህም ሕገ ወጦች ይባላሉ።

ምሳሌ፡- አብ፡ አቡሁ፣ አቡሆሙ፣ አቡሃ፣ አቡሆን፣ አቡከ፣ አቡክሙ፣ አቡኪ፣ አቡክን፣ አቡየ፣ አቡነ

**ምልማድ ፫**

ሀ, የሚከተሉትን ስሞች በአስሩ መራሕያን ዘርዝሩ።

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዜና | ቅዳሴ | ፍሬ | መንግሥት | መላእክት | አግብርት | ርእስ | ብረከ | አብራክ |
| ጦማር | ሀቅል | አብህርት | ዘባን | ዘባናት | አዕይንት | ፆም | አፅዋም | ስምዕ |
| ሲመት | እክል | ደብር | አድባራት | ልብስ | ዐራት | | | |

ለ, የሚከተሉትን ዐ/ነገሮችወደ ግእዝ ለዉጡ።

1. ቅዳሴውን ሰማን።
2. የጥበብ ሃገሯ ወዴት ነው?
3. አምላኬ ሆይ ብርሃኔ አንተ ነህ።
4. ቅዱስ ሥጋውን በላን።
5. ማርታና አየለ ለእግዚአብሔር ዘመሩ።

ሐ, የሚከተሉትን አዛምዱ።

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> | |
|---|---|---|
| 1, ውእቱ | ሀ, ወልዱ | ኀ, ሰኮናሆን |
| 2, ውእቶሙ | ለ, እኁሁ | ነ, ከዋክብቲክሙ |
| 3, ይእቲ | ሐ, አብያቲሆን | አ, ቤቶሙ |
| 4, አንትሙ | መ, አእባኒከ | |
| 5, አንተ | ሠ, ርእሳ | |
| 6, ውእቶን | ረ, አፍራሲየ | |
| 7, አንቲ | ሰ, ዘመድነ | |
| 8, አንትን | ቀ, አዝማዲነ | |
| 9, አነ | በ, ልሳንኪ | |
| 10, ንሕነ | ተ, ገቦየ | |

## ፩.፺ መስተዋድዳን ቀለማት

በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ጊዜ ከስም እና ከግስ በተጨማሪ ከስም ላይ ወይም ከግስ ላይ እየወደቁ የንግግሩን/የጽሑፉን ሐሣብ የተሟላ እንዲሆን የሚያደርጉ ቀለማት አሉ፡፡ እነዚህም በግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አገባብ ይባላሉ፡፡አገባባት በሶስት የሚከፈሉ ሲሆን ዐቢይ አገባብ፣ ንዑስ አገባብ፣ ደቂቅ አገባብ ይባላሉ፡፡ በግእዝ ሰዋስው ደቂቅ አገባብ የተባሉት በአማርኛ መስተዋድዳን የሚባሉት ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ከሶስቱም አገባባት የተውጣጡ ቃላት ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

| <u>አገባብ</u> | <u>የአማርኛ ፍቺ</u> | <u>አገባብ</u> | <u>የአማርኛ ፍቺ</u> |
|---|---|---|---|
| ዲበ፣ላዕለ፣መልዕልተ | በ _ ላይ | ዝንቱ/ዝ | ይህ |
| ታሕተ፣መትሕተ | በ _ ታች | ዛቲ | ይህች |
| ማዕከለ | መካከል/በ _ መካከል | እሉ | እኚህ |
| ውስተ | ውስጥ/በ _ ውስጥ | እላ | እኚህ |
| ቅድመ | በፊት/በ _ ፊት | ዘ፣እለ፣እንተ | የ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ድኅረ | በኋላ/በ _ ኋላ | በይነ፣በእንተ፣እንበይነ | ስለ |
| እስከ(እስከነ) | እስከ | በይነዝንቱ፣በእንተዝንቱ | ስለዚህ |
| ኀበ | ወደ/ዘንድ | እምድኅረዝንቱ | ከዚህ በኋላ |
| መንገለ | ወደ | እስመ / አምጣነ / አኮኑ | ና |
| አምሳለ | እንደ | መጠነ | ያህል |
| ከመ | እንደ | ዳዕሙ / ባህቱ | ነገር ግን |
| ምስለ | ጋር | አላ | እንጅ |
| እንበለ | ያለ፣በቀር | ወሚመ/አው | ወይም |
| እም/እምነ | ከ | ናሁ | እነሆ |
| እመ | ቢ፣ባ፣ብ፣ሊ፣ከ ፣ኪ | እፎ | እንዴት |
| እንዘ | እየ፣ሲ፣ሳ፣ስ | ጌሠም | ነገ |
| ሶበ/አመ | በ _ ጊዜ | ዮም/ይዕዜ | ዛሬ |
| ጊዜ | በጊዜ/በ _ ጊዜ | ትማልም | ትላንት |

ምሳሌ ፡- በሚከተሉት ዐ/ነገሮች ውስጥ መስተዋድዳን ቀለማቱን አስተውሉ

ሀ, አመ ተሰቅለ ክርስቶስ መልዕልተ መስቀል ፀሐይ ጸልመ፡፡

ለ, ናሁ ተወልደ ዮም ቤዛ ኵሉ ዓለም በከመተነበየ ኢሳይያስ ነቢይ።

ሐ , ነግሠ ሞት እምነ አዳም እስከ ሙሴ

መ , አመ ይመጽዕ ወልድኪ ምስለ አእላፍ መላእክቲሁ።

ሠ , ሰአሊ ለነ ማርያም በቅድሜሁ።

ረ , ተዐውቀ ዝንቱ ብእሲ በኀበ ሊቃውንትአምጣነ ምሁር ውእቱ።

**<u>የመስተዋድዳን ዝርዝር በመራሕያን</u>**

መስተዋድዳን ቀለማት የሚዘረዘሩ እና የማይዘረዘሩ አሉ።ከማይዘረዘሩት ለምሳሌ እም፣እስከ የሚዘረዘሩት መስተዋድዳን ግን በአሥሩ መራሕያን በአገናዛቢ ቅጽል አማካኝነት ይዘረዘራሉ።(ስለ አገናዛቢ ቅጽል የስም ዝርዝር በመራሕያን የሚለውን ክፍል አስታውሱ።) በሚዘረዘሩበት ጊዜም አብዛኛዎቹ መድረሻቸውን ወደ ኀምስ ይለውጣሉ።

ምሳሌ ፡- 1, መንገለ

| | | |
|---|---|---|
| መንገሌሁ =ወደ እርሱ | መንገሌከ =ወደ አንተ | መንገሌየ =ወደ እኔ |
| መንገሌሆሙ=ወደ እነርሱ | መንገሌክሙ =ወደ እናንተ | መንገሌነ = ወደ እኛ |
| መንገሌሃ=ወደ እሷ | መንገሌኪ =ወደ አንቺ | |
| መንገሌሆን=ወደ እነርሱ | መንገሌክን =ወደ እናንተ | |

2, ቅድመ

| | | |
|---|---|---|
| ቅድሜሁ =በፊቱ | ቅድሜከ =በፊትህ | ቅድሜየ = በፊቴ |
| ቅድሜሆሙ =በፊታቸው | ቅድሜክሙ =በፊታችሁ | ቅድሜነ =በፊታችን |
| ቅድሜሃ =በፊቷ | ቅድሜኪ =በፊትሽ | |
| ቅድሜሆን =በፊታቸው | ቅድሜክን=በፊታችሁ | |

ከኀምስ ውጭም መድረሻቸውን ወደ ራብዕ እና ሳልስ በመቀየርየሚዘረዘሩ አሉ።

ምሳሌ ፡- 1, ከመ

| | | |
|---|---|---|
| ከማሁ = እንደ እርሱ | ከማከ = እንደ አንተ | ከማየ = እንደ እኔ |
| ከማሆሙ = እንደ እነርሱ | ከማክሙ = እንደ እናንተ | ከማነ = እንደ እኛ |
| ከማሃ = እንደ እርሷ | ከማኪ = እንደ አንቺ | |
| ከማሆ = እንደ እነርሱ | ከማክን = እንደ እናንተ | |

2, ውስተ

| | | |
|---|---|---|
| ውስቴቱ = በውስጡ | ውስቴትከ = በውስህ | ውስቴትየ = በውስጤ |
| ውስቴቶሙ = በውስጣቸው | ውስቴትክሙ = በውስጣችሁ | ውስቴትነ = በውስጣችን |
| ውስቴታ = በውስጧ | ውስቴትኪ = በውስጥሽ | |

ውስቴቶን = በውስጣቸው ውስቴትክን = በውስጣችሁ

**ምልማድ ፬**

፩, የሚከተሉትን ተርጉሙ።

ሀ , ወይቤላ መልአከ ኢትፍርሒ ማርያም እስመ ረከብኪሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር

ለ , ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪማርያም እምነ ናስተበቍዐኪ

ሐ , ናሁ እም ይእዜሰ ያስተበጽዑኒ ኵሉ ትውልድ

መ , እኩሕደከ ሰይጣን በቅድመ ዛቲ ቤተክርስቲያን

ሠ , አእምሩ ከመ ኮነ እግዚአብሔር ኄር

፪ , የሚከተሉትን መስተዋድዳን ቀለማት ዘርዝሩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዲበ | ድኅረ | እለ | ታሕተ |
| ምስለ | ባሕቲት | ማእከለ | ኀበ |
| እምነ | እንተ | እንበለ | አምሳለ |

## የ"ለ" እና የ"በ" ዝርዝር

"ለ" እና "በ" ቍጥራቸው ከመስተዋድዳን ሲሆን ትርጉማቸውም እንደሚከተለውይሆናል።

<u>የ"ለ" ትርጉም</u>

- በቁም ቀሪ (ለ) ምሳሌ :- ሰድ ሎቱ መጽሐፎ ለእኁከ
- ዘርፍ አያያዥ (የ) ወረዱ ግብጸ ዉሉዱ ለያዕቆብ
- ተጠቃሽ ተሳቢ(ን) ንሴብሖ ለአምላክነ
- አዳማቂ(ትርጉም የለሽ) ዘጸምዐ ለይምጻዕ ኀቤየ

<u>የ"በ" ትርጉም</u>

- በቁም ቀሪ ምሳሌ:- ኤልያስ ዐርገ በሰረገላ እሳት።
- ለ ተናፀሩ ገጽ በገጽ።
- በ _ጊዜ በምንዳቤየ ተዘከርኩከ።

**"ለ" እና** "በ" በአሥሩ መራሕያን እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሎቱ | ለክሙ | ቦቱ | ብክሙ |
| ሎሙ/ሎቶሙ | ለኪ | ቦቶሙ/በሙ | ብኪ |
| ላቲ | ለክን | ባቲ | ብክን |
| ሎን/ሎቶን | ሊተ/ልየ | ቦቶን/ቦን | ብየ |
| ለከ | ለነ | ብከ | ብነ |

የ"ለ" እና "በ" ዝርዝሮ ች በዐ/ ነገር ውስጥ ሁለት ዓይነት አገልግሎት ያላቸው ሲሆን ከመስተዋድድ ዝርዝርነታቸው በተጨማሪ የነባር አንቀጹ "ቦ" እና "ሎ" ዝርዝሮችም ናቸውና የነባር አንቀጽነት ትርጉም አላቸው።

<u>**፩ መደበኛ ሆነው ሲያገለግሉ**</u> :- መደበኛ ሆነው የሚያገለግሉትም ከግሥ ቀድመው ከመጡ ነው። በዐ/ነገሩ ውስጥ ማሰሪያ አንቀጽ ከሌለ ነባር አንቀጽ ሆነው ያገለግላሉ። የሚኖራቸውም ትርጉም እንደሚከተለው ይሆናል።

<u>**የ"ለ" ዝርዝር**</u> ሎቱ= ለእርሱ፣አለው፣አለለት፣ኖረለት፣ነበረለት፣ይገባዋል

ሎሙ/ሎቶሙ= ለእነርሱ፣አላቸው፣አለላቸው፣ኖረላቸው፣ነበረላቸው፣ይገባቸዋል

ላቲ= ለእርሷ፣አላት፣አለላት፣ኖረላት፣ነበረላት፣ይገባታል

ሎን/ሎቶን= ለእነርሱ፣አላቸው፣አለላቸው፣ኖረላቸው፣ነበረላቸው፣ይገባቸዋል

ለከ= ለአንተ ፣አለህ፣አለልህ፣ኖረልህ፣ነበረልህ፣ይገባሃል

ለክሙ= ለአናንተ ፣አላችሁ፣አለላችሁ፣ኖረላችሁ፣ነበረላችሁ፣ይገባችኋል

ለኪ= ለአንቺ ፣አለሽ፣አለልሽ፣ኖረልሽ፣ነበረልሽ፣ይገባሻል

ለክን= ለአናንተ ፣አላችሁ፣አለላችሁ፣ኖረላችሁ፣ነበረላችሁ፣ይገባችኋል

ለነ= ለእኔ፣አለኝ፣አለልኝ፣ኖረልኝ፣ነበረልኝ፣ይገባኛል

ሊተ/ልየ= ለእኛ፣አለን፣አለልን፣ኖረልን፣ነበረልን፣ይገባናል

**የ"በ" ዝርዝር** ቦቱ= በእርሱ፣አለው፣አለበት፣ኖረበት፣ነበረበት፣ነበር፣አለ

ቦቶሙ/ቦሙ= በእነርሱ፣አላቸው፣አለባቸ፣ኖረባቸው፣ነበረባቸ፣ነበሩ፣አሉ

ባቲ= በእርሷ፣አላት፣አለባት፣ኖረባት፣ነበረባት፣ነበረች፣አለች

ቦቶን/ቦን= በእነርሱ፣አላቸው፣አለባቸ፣ኖረባቸው፣ነበረባቸ፣ነበሩ፣አሉ

ብከ= በአንተ፣አለህ፣አለብህ፣ኖረብህ፣ነበረብህ፣ነበርህ፣አለህ

ብክሙ= በእናንተ፣አላችሁ፣አለባችሁ፣ኖረባችሁ፣ነበረባችሁ፣ነበራችሁ፣አላችሁ

ብኪ= በአንቺ፣አለሽ፣አለብሽ፣ኖረብሽ፣ነበረብሽ፣ነበርሽ፣አለሽ

ብክን= በእናንተ፣አላችሁ፣አለባችሁ፣ኖረባችሁ፣ነበረባችሁ፣ነበራችሁ፣አላችሁ

ብየ= በእኔ፣አለኝ፣አለብኝ፣ኖረብኝ፣ነበረብኝ፣ነበርሁ፣አለሁ

ብነ= በእኛ፣አለን፣አለብን፣ኖረብን፣ነበረብን፣ነበርን፣አለን

**ምሳሌ ፡-** ዘየአምን ብየ ቦ ሕይወት ዘለዓለም።

ብከ ንወግዖሙ ለከሎሙ ፀርነ።

ብኪ ወጽዐ አዳም እምሲዖል።

ለከ ንፌኑ ልዑለ ውዳሴ።

ሎቱ ስብሐት።

ለነ ለአግብርቲከ ሀበነ አዕይንተ አእምሮ።

**፪ ተቀባይ ሆነው ሲያገለግሉ፡-** የ"ለ" እና "በ" ዝርዝሮች ተቀባይ ሆነው እንዲያገለግሉ ሁልጊዜም ከግስ በኋላ መምጣት አለባቸው። የሚኖራቸው ትርጉምም እንደሚከተለው ይሆናል።

| የ"ለ" ዝርዝር ች | | የ"በ" ዝርዝር ች | |
|---|---|---|---|
| ሎቱ= ለት | ለክሙ= ላችሁ | ቦቱ= በት | ብክን =ባችሁ |
| ሎሙ/ሎቶሙ= ላቸው | ለኪ= ልሽ | ቦቶሙ/ቦሙ= ባቸው | ብኪ = ብሽ |
| ላቲ= ላት | ለክን= ላችሁ | ባቲ= ባት | ብክን =ባችሁ |
| ሎን/ሎቶን= ላቸው | ሊተ/ልየ= ልኝ | ቦቶን/ቦን= ባቸው | ብየ =ብኝ |
| ለከ= ልህ | ለነ= ልን | ብከ= ብህ | ብነ =ብን |

**ምሳሌ ፡-**ሰገደ ላቲ= ሰገደላት

ፈነወ ላቲ= ላከላት

ብልዐ ሊተ= ብላልኝ

አምጽዐ ሎሙ= አመጣላቸው

አሕየወ ሎቱ= አዳነለት

መጽዑ ቦሙ= መጣባቸው

ሞተ ብኪ አቡኪ= አባትሽ ሞተብሽ

አፍለሰ ቦሙ= አሸሸባቸው

ማሰነ ብነ ንዋይነ= ገንዘባችን ጠፋብን

አርኀቀ ብከ= አራቀብህ

**ማስታወሻ፡-** "ቦ" ነባር አንቀጽ ሲሆን በመኖር ግሥ ይነገራል። (ነው፣ነበር፣አለ) በአሥሩ መራሕያን ሲዘረዘር እንደ መስተዋድዱ "በ" ይዘረዘራል።ይህንንም ከላይ አይተናል።"ቦ" አሥሩንም ዝርዝሮቹን ተክቶ ይነገራል።

ምሳሌ፡-ሀ, ቦ ጊዜ ለኵሉ።(የ "ቦ" ትርጉም አለው)

ለ , ቦ አዳም ውስተ ገነት መጠነ ሰብዐቱ ዓመት።(የ "ቦ" ትርጉም ነበረ)

ሐ, ቦ እለ ይብሉከ ዮሐንስሃ መጥምቅ።(የ "ቦ" ትርጉም አሉ)

የ "ቦ" ዝርዝሮች አፍራሻቸው አል ሲሆን የ"ለ" ዝርዝሮች ግን አፍራሽ የላቸውም።

ምሳሌ ፡- ሀ, አልብነ ንጉሥ ዘእንበለ ቄሣር

ለ, አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ

ሐ, አልቦ ዘያድኅነከ እምእዴየ

**የ"ነ" ዝርዝር**

"ነ " ምንም እንኳ መስተዋድድ ባይሆንም በአገናዛቢ ቅጽል አማካኝነት በአሥሩ መራሕያን ይዘረዘራል። ክፍሉም በተውሳከ ግስ ምድብ መስተአምራዊ አንቀጽ አጎላማሽ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ነዋ(ናሁ) =እነሆ | ነየከ =እነሆህ | ነየ =እነሆኝ |
| ነዮ/ነዮሙ =እነኋቸው | ነየክሙ =እነኋችሁ | ነየነ =እነኆን |
| ነያ =እነኋት | ነየኪ =እነሆሽ | |

ነዮን =እነኀቸው ነየከን =እነኀችሁ

ምሳሌ :-ወይቤሎሙ ጲላጦስ ለአይሁድ ነዋ ንጉሥክሙ
ነየ አመቱ ለእግዚአብሔር
ነያ እምከ ነዋ ወልድኪ

**ምልማድ ፫**

፩ የሚከተሉትን ዐ/ነገሮች ተርጉሙ

ሀ, አንተ ስቡሕ አንተ
ለ, አንቲ ውእቱ ሰዋስው
ሐ, አንተ ሖርከ ምስሌሃ
መ, አነ አእመርኩ ኪያሁ
ሠ, ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ለክርስቶስ በአማን
ረ, አንተ ውእቱ ብርሀኑ ለዓለም
ሰ, አንተ ውእቱ ወልዱ ለአብ
ቀ, ገብርኤል ሰብሐ ኪያሃ
በ, ቅድስት ሐና እማ ይእቲ ለእግዝእትነ ማርያም
ተ, ካሀናት ውእቶሙ አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር
ነ, ማርታ ወዳዊት እኩያን እሙንቱ

፪ የሚከተሉትን አስማምታችሁአሟሉ

ሀ, አነ______________ (መጽዐ) ኀቤሁ
ለ, ቶማስ ወማርታ ______________ (ቀተለ) አርዌ
ሐ, አንተ ውእቱ _________________ (አብ) ለሐሰት
መ, ዛቲ ይእቲ ___________________(ምዕራፍ) ለዓለም
ሠ, ኤሊያስ ሖረ _____________(ባሕቲት)

## ፩.፫ የቃላት ጥናት
## ስመ ክፍላተ አካላት

በዚህ ክፍል የሰው ልጆችን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች በግእዝ ያላቸውን ስያሜ እንመለከታለን:: ለማጥናት ይረዳን ዘንድ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለን እናጠናቸዋለን።

፩ ከተከሻ በላይ የሚገኙ የሰውነት ክፍሎች

| ነጠላ | ብዙ | የአማርኛ ትርጉም | ነጠላ | ብዙ | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|---|---|---|
| ርእስ | አርእስት | ራስ | ድማህ | | መሀል ራስ |
| ስእርት | ስእርታት | ፀጉር | ጽፍሮ | | ሹሩባ |
| ናላ | | አናት | ድንጉዝ | | ጥቅል ስራ |
| ሲበት | | ሽበት | ድምድማ | | የተበጠረ ጎፈሬ |
| ገጽ | | ፊት | ከዋላ | | ኋላ |
| መልታሕት | | ፊት | መልታሕ | መላትሕ | ጉንጭ |
| ፍጽም | | ግንባር | ዐይን | አዕይንት | ዐይን |
| ቀርነብ | ቀራንብት | ቅንድብ | ምጉንጽ | | ሽፋል |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አንፍ | አእናፍ | አፍንጫ | አፍ | አፈው | አፍ |
| ከንፈር | ከናፍር | ከንፈር | ስን | አስናን | ጥርስ |
| መንሰከ/ጥረስ | | መንጋጋ | ትናግ | | ላንቃ |
| ልሣን | ልሣናት | ምላስ/አንደበት | ቃል | ቃላት | ድምፅ |
| እስትንፋስ | እስትንፋሳት | ትንፋሽ | ጉርዔ | ጉርዔት | ጉሮሮ |
| ምራቅ | | ምራቅ | ፋጻ | | ፉጨት |
| ጉማ/ጉሕና | | ጎርናና ድምፅ | ቃና | | የዜማ ድምፅ |
| ሕልቅ | | አገጭ | ጽሕም | | ጢም |
| ክሳድ | ክሳውድ | አንገት | መትከፍ | መታክፍት | ትክሻ |
| አቀል | | አእምሮ | አቅል | | ጥበብ/ብልሀት/ሀሳብ |

፪ ከወገብ በላይ የሚገኙ የሰውነት ክፍሎች

| ነጠላ | ብዙ | የአማርኛ ትርጉም | ነጠላ | ብዙ | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|---|---|---|
| ዘባን | ዘባናት | ጀርባ | እንግድአ | እንግድአት | ደረት |
| ሕፅን | | ብብት | እድ | አእዳው/እደው | እጅ |
| መዝራዕት | መዛርዕ | መዳፍ | ኩርናዕ | ኩርናዕት | ክርን |
| እመት | እመታት | ክንድ | እራሕ | እራሓት | መሀል እጅ |
| አፃብዕ | አፃብዕ | ጣት | ጽፍር | ጽፍራት | ጥፍር |
| ጥብዕ | ጥብዐት | ጡት | ገቦ | ገቦአት | ጎን |
| ከር/ከበድ | ከርሳት | የምግብ ቋት | ልብ | ልቡና | ልብ |
| ሕሊና | | ሀሳብ | አማዑት | | አንጀት |
| መሳውዕ | | ጅማት | ንዋየ ውስጥ | | ሆድ ዕቃ |
| ሐቋ | ሐቊያት | ወገብ | | | |

3 ከወገብ በታች የሚገኙ የሰውነት ክፍሎች

| ነጠላ | ብዙ | የአማርኛ ትርጉም | ነጠላ | ብዙ | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|---|---|---|
| ሕንብርት | | እንብርት | ኩሊት | ኩሊያት | ኩላሊት |
| ሐሞት | | አሞት | እኪት | | የወንድ ብልት |
| አኒን | | ቆለጥ | ሕልጽ | | የሴት ብልት |
| ከረቤዛ | | ሴት የምትገረዝበት | ዳዕሌ | | ዳሌ |
| ቁይጽ | አቁያጽ | ጭን | ብረክ | አብራክ | ጉልበት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ከቢ | | ባት | እግር | አእጋር/እገር | እግር |
| ሰኰና | ሰኳንው | ተረከዝ | መከየድ | | ጫማ |
| ሌሎች ከሰውነት ክፍል ጋር የሚገናኙ ስሞች | | | | | |
| ቆም | | ቁመት | መልክእ | | መልክ |
| ቀይሕ | ቀይሐን | ቀይ | ጸሊም | ጸሊማን | ጥቁር |
| ነዊኀ | ነዊኃን | ረዥም | ሐጺር | | አጭር |
| ሰንበል | | ዛላ/ውበት | ዐፅም | አዕፅምት | አጥንት |
| ግዙፍ | | ወፍራም | ላሕይ | | ደም ግባት |
| ሐፍ | | ወዝ | ዝንየት | | ፍትወተ ሥጋ |

ምሳሌዎች፡-ተንሥእ እግዚኦ አምላኪየ ወአድኅነኒ እስመ አንተ ቀሰፍኮሙ እለ ይጻረሩኒ በከንቱ፡፡ ሰነኒሆሙ ለኃጥዓን ሰበርከ፡፡

ወኢየኀድሩ እኩያን ምስሌከ፡፡ ወኢይነብሩ ዐማፅያን ቅድመ አዕይንቲከ፡፡

ሰላም ለርእስኪ በቅብአ ቅዳሴ ርሑስ፡፡ አኮ አኮ በቅብዐ ደነስ፡፡

ሰላም ለእንግድአኪ ለእሳተ መለኮት ምርፋቁ ዘይቄድስ ነፍሰ ወያጥዒ ሞቁ፡፡

እደውየ ይገብራ መሰንቆ ወአፃብየ ያስተዋድዳ መዝሙረ፡፡

ሰላም ለኩርናዕከ ኩርናዐ ክቡድ አንበሳ ዘቀጥቀጠ ኩሎን አርእስተ ስቡሐን እንሰሳ፡፡

ምልማድ ፮ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት በተስማሚው ባዶ ቦታ ላይ ሙሉ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ስእርት | መዝራእት | እስኪት | ሲበት | ጽፍር | |
| አእጋሪከ | ጉርዔከ | ከርስ | ሰኰና | አቅልየ | |
| ጥብ | ዝንየት | ላህይ | ነዊህ | አንጉዕ | ልብከ |

1. ብእሲት ቦን ዐብይ _________ ወብእሲሰ ንዑስ ውእቱ፡፡
2. ሰላም ለ________ከንፈ ነፋስ እለ ይረውጻ አብያተ ግፉዓን ከመ የሐውጻ፡፡
3. ._____________ ትእምርተ እድሜ ውእቱ፡፡
4. .___________ ቦ እም ላዕለ ኩሎን ክፍላተ ሕዋሳት፡፡
5. ሶበ ረከበኒ_______ ኢይበውእ ውስተ ቤተክርስቲን፡፡
6. ያዕቆብ ይትበሀል አኃዜ __________ ውስተ መጽሐፍ ቅዱስ፡፡
7. _________ ይብዕድ ብእሲ እም ብእሲት ፡፡
8. __________ ቦ ላዕለ አእዳው፡፡
9. በ _________ አሐሊ ሰናየ ወእኩየ አቅለ፡፡
10. ሰላም _______ ዘድምጸ ጉሕናሁ መደንግጽ፡፡

# ምዕራፍ ፪

## ሥርዓተ ንባብ ዘልሣነ ግእዝ

የግእዝ ቋንቋ የራሱ የሆነ የተወሰነ ሥርዓተ ንባብ አለው፡፡ይህ የንባብ ሥርዓቱ ከተፋለሰ ቋንቋው ለዛ ያጣል፡፡አንባቢውም ሆነ አድማጩ ምሥጢሩን ስለማይረዳው ቃሉ ትርጉም ያጣል፡፡ ስለዚህ የግእዝ መጻሕፍትን ሁሉ ለማንበብ የግእዝ ቋንቋን ሥርዓተ ንባብ መማር ይጠበቅብናል፡፡በግእዝ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንዱ እና ትልቁ ክፍል የንባብ ህግጋቱነው፡፡በግእዝ ቋንቋ ሶስት ዓይነት የንባብ ዓይነቶች አሉ፡፡ ይህም አከፋፈል በንባብ ጊዜ ከድምፅ አወጣጥ አንጻር ነው፡፡

**<u>፩ ግእዝ ንባብ</u>** ፡- ይህ የንባብ ዓይነት ቃልን ከቃል እየለዩ የሚነበብበትየንባብ ዓይነት ሲሆን በአብነት ትምህርት ቤቶች የንባብ ትምህርት የመጀመሪያው የንባብ ደረጃ ነው፡፡ ፊደል የለየ ተማሪ የሚያነበው የመጀመሪያው የንባብ ዓይነት ነው፡፡ ሲነበብም ፊደልን ከፊደል እየለዩ በዝግታ ሳብ ሳብ እያለ የሚነበብ የንባብ ዓይነት ነው፡፡

**<u>፪ ውርድ ንባብ</u>** ፡- ይህ ሁለተኛው የንባብ ደረጃ ግእዝ ንባብን አንብቦ የጨረሰ ተማሪ የሚያነበው ቀጣይ ደረጃ ሲሆን የኅዘን ዜማ መልክ ያለው የንባብ ዓይነት ነው፡፡ሲነበብም ቃላትን ከቃላት እየለዩ ነው፡፡የግእዝ ንባብ ጐተት ዝግ ይል የነበረውን ሳብ ሳብ በማድረግ ይነበባል፡፡ሳቢ እና ተሳቢው ተነሽ እና ወዳቂው አንቀጹ እና አንቀጽ አጐላማሹ በየአመሉ እየተለየ የሚነበብበት የንባብ ዓይነት ነው፡፡

**<u>፫ ቁም ንባብ</u>** ፡- ከውርድ ቀጥሎ ሶስተኛው የንባብ ደረጃ ሲሆን ያለአንዳች ችግር ሕግጋተ ንባባትን ተነሽ ተጣዩን ወዳቂና ሰያፉን ጠንቅቆ በመለየት ጠበቅ ያዝ ለቀቅዘለግ ፈጠን እየተደረገ የሚነበብበት የንባብ ደረጃ ነው፡፡ ይህ የንባብ ዓይነት ዘወትር በቤተክርስቲያን በሊቃውንት ፊት ቅዱሳት መጻሕፍት የሚነበቡበት የንባብ ዓይነት ነው፡፡

### ፪.፩ የንባብ ዓይነቶች

በግእዝ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የታወቁት የንባብ ዓይነቶች አራት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

| | |
|---|---|
| ፩, ተነሽ | ፫, ወዳቂ |
| ፪, ሰያፍ | ፬, ተጣይ |

አንድን ቃል የአነባበብ ሥርዓቱን ለማወቅ የሚከተሉትን መለያዎች እንጠቀማለን

- መድረሻ ቀለም
- የሆሄያት ተጽዕኖ
- ተነባቢ ቀለም
- የቃሉ ባህርይ(ስም ወይም ግስ መሆኑ) በዚህ ክፍል ለአካሄድ እንዲያመቸን ከግስ ውጭ የሆኑትን ሁሉ ስም እንላቸዋለን

**<u>፩ ተነሽ ንባብ</u>**

ተነሽ ንባብ የሚባለው እንደ ቁጣ ቃል የሚነገር ተፈላጊውን ቀለም አንስቶ አንዝሮ የሚነበብ ንባብ ነው፡፡ተነስተው የሚነበቡ ቃላትን ለመለየት የሚከተለውን ዘዴ እንጠቀማለን፡፡

**<u>ሀ, መድረሻ ቀለም</u>** ፡- ተነስተው ሊነበቡ የሚችሉ ቃላት በአምስቱ የሆሄ ስልት የጨረሱ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡እነዚህም፡-
ግእዝ፣ካዕብ፣ሳልስ፣ራብዕ እና ሳብዕ ናቸው፡፡በእነዚህ ያልደረሰ ቃል ፈጽሞ ሊነሳ አይችልም፡፡

ምሳሌ፡-በግእዝ፡ ቆመ፣ገብረ፣ሐቀለ፣አንፈርዐፀ፣ሰበከ
በካዕብ፡ ቆሙ፣ገብሩ፣ሐቀሉ፣አንፈርዐፁ፣ሰበኩ
በሣልስ፡ ቁሚ፣ግበሪ፣ ሕቅሊ፣ስብኪ፣ቀድሲ
በራብዕ፡ ቆማ፣ ቀደሳ፣ አእመራ፣ ያእምራ
በሳብዕ፡ አሥመረቶ፣ንሴብሖ፣ይግብሮ

በግእዝ ወይም በሌሎቹ የጨረሰ ሁሉ ግን ተነስቶ ይነበባል ማለት አይደለም፡፡ለምሳሌ የሚከተሉትን ህገወጦች መመልከት እንችላለን፡፡
ህየ፣እወ፣ሠለስተ፣ክልዔተ፣አርባዕተ — በግእዝ ቢጨርሱም ተነስተው አይነበቡም፡፡
አሐዱ፣ክልዔቱ፣ሠለስቱ፣አርባዕቱ — በካዕብ ቢጨርሱም አይነሱም፡፡

**<u>ለ, ተነባቢ ቀለም</u>** ፡- የተነሽ ቃላት ተነባቢ ቀለማቸው ቅድመ መድረሻቸው ነው፡፡ ቅድመ መድረሻቸው ቆጣ ነዘር ብሎ ይነበባሉ፡፡
ምሳሌ፡ አእመረ፣ወረደ፣ቀተለ፣ሐወጸ

**<u>ሐ, የቃል ክፍል</u>** ፡- በአብዛኛው ተነስተው የሚነበቡ ቃላት ግሶች ናቸው፡፡
ማስታወሻ፡- ሶስት ቀለም ያላቸው በግእዝ ጀምረው ቅድመ መድረሻቸው ሳድስ በሆኑ ግሶች ሳድስ ቀለሙ ተውጦ ይነበባል፡፡

ምሳሌ፦ ገብረ፣ፈርሐ፣መርሐ፣መጽዐ

ኀረየ ዐሥርተ ወክልኤተ አርድእተ

አቅረብኩ ለከ እሳተ ወማየ ደይ እዴከ ኀበ ዘፈቀድከ

ንሴብሐከ እግዚኦ

**፪ ተጣይ ንባብ**

ተጣይ ቀለማት ሲነበቡ እንደ ወዳቂ ቀለም ያዝ ለቀቅ በማድረግ ነው፡፡

***ሀ, መድረሻ ቀለም*** ፦ ተጣይ ቀላት የሚጨርሱት በሳድስ ቀለም ብቻ ነው፡፡

ምሳሌ፦ ቅዱስ፣ ኅሩይ፣ መንሱት፣ መንበር፣ ሰዋስው፣ ልብ፣ ዮም፣ ጾም

**ለ, ተነባቢ ቀለም** ፦ የተጣይ ቀለም ተነባቢ ቀለሙ ቅድመ መድረሻው ስለሆነ ይህን ቀለም ያዝ ቆየት በማድረግ ይነበባሉ፡፡

**ሐ, የቃል ክፍል** ፦ ተጣይ ቃላት በአብዛኛው ስሞች ናቸው፡፡ ከግስ የወጡ ዘሮች በአብዛኛው ተጥለው ይነበባሉ፡፡

ምሳሌ፦ ኅሩያን፣ ቡሩክ፣ ሲሳይ፣ መላእክት

ፃድቃን ወሰማዕት ጽኑዓን በሃይማኖት

ንጉሥ ወካህናት ክቡራን በኀበ እግዚአብሔር

ማስታወሻ፦ የተጣይ ቃላት ሳድስ ቀለማት ተከታትለው ሲመጡ ቅድመ መድረሻቸው ተውጦ ይነበባሉ፡፡

ምሳሌ፦ወርቅ፣ ፍቅር፣ ምድር፣ ምግብ፣ ዘርዕ፣ ቅድስት፣ ትስብእት

**፫ ወዳቂ ንባብ**

ይህ የንባብ ዓይነት ተፈላጊውን ቀለም ያዝ ቆየት በማድረግ ይነበባል፡፡ ወዳቂ ንባብ ወዳቂ ዜማ ባለው ድምጸ ማኅዘኒ ይነበባል፡፡

***ሀ, መድረሻ ቀለም*** ፦ የወዳቂ ቀለማት መድረሻ ቀለማት ሰባቱም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ምሳሌ፦** በግእዝ፦ ሀየ፣ አሐደ፣ ክልዔተ

በካዕብ፦ ኰሉ፣ ብሔሩ፣ ዝንቱ፣ እሙንቱ፣ እማንቱ

በሳልስ፦ ቀታሊ፣ ገባሪ፣ ዛቲ፣ ኖላዊ፣ ነጋሢ፣ ዜናዊ

በራብዕ፦ ዜና፣ መና፣ ሠረገላ፣ ተድላ፣ መከራ፣ ሀገራ

በኀምስ፦ አይቴ፣ ምናኔ፣ ሥላሴ፣ ልምላሜ፣ ትካዜ

በሳድስ፦ ዝ ብቻ ነው(በሳድስ ወዳቂ ዝ ብቻ ነው)

በሳብዕ፦ ከበሮ፣ አእምሮ፣ እፎ፣ ተዋህዶ

**ለ, ተነባቢ ቀለም** ፦ በወዳቂ ንባብ ጊዜ ተነባቢ ቀለሙ መድረሻ ቀለሙ ነው፡፡ተነባቢ ቀለሙን ያዝ ቆየት በማድረግ ይነበባል፡፡

**ሐ, የቃል ክፍል** ፦ ወድቀው የሚነበቡ በአብዛኛው ስሞች ናቸው፡፡ በዚህ ትምህርት ከግስ ውጭ ያሉትን ሁሉ በስም ስር መድበናቸዋል

**፬ ሰያፍ ንባብ**

ይህ የንባብ ዓይነት ተፈላጊውን ቀለም እንደ ተነሽ ንባብ አስቀጥቶ አንዝሮ ይነበባል፡፡

***ሀ, መድረሻ ቀለም*** ፦ ሰያፍ ንባብ በሳድስ ብቻ ይጨርሳል፡፡

**ለ, ተነባቢ ቀለም** ፦ ተነባቢ ቀለሙ ቅድመ መድረሻው ነው፡፡

**ሐ, የቃል ክፍል** ፦ ተሰይፈው የሚነበቡ ስሞችም ግሶችም ናቸው፡፡

ምሳሌ፦ አእመረት፣ ቀተለት፣ ይወርድ፣ ይገብር፣ እቀትል፣ ቅትል፣ገበር፣ንላዕ

ኢሳያስ፣ ቶማስ፣ ገብርኤል፣ ጴጥሮስ፣ ዳንኤል፣ ቴዎፍሎስ

ገብርኤል ሰብሐ ኪያሃ

ንፁም ፆመ ወናፍቅር ቢጸነ

ማስታወሻ፦ ሰያፍ እና ተነሽ በአነባበብ አንድ ናቸው የሚለያዩት በመድረሻ ቀለማቸው ነው፡፡

ወዳቂ እና ተጣይ ሥርዓተ ንባባቸው አንድ ነው ቢባልም በተነባቢ ቀለም እና በመድረሻ ቀለም ይለያያሉ፡፡

**፪.፪ ተናባቢ ንባብ**

ሁለት የተለያዩ ቃላት በዘርፍ እና በባለቤትነት በአንድ ትንፋሽ እንደ እንድ ቃል ሲነበቡ ተናባቢ ንባብ ይባላል። ተናባቢ ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት መድረሻቸው ሳድስ፣ ሣልስ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ እና ሳብዕ የሆኑ ቃላት ብቻ ናቸው።ይህንንም በምሳሌ እንመለከተዋለን፦

ሀ. በሳድስ የደረሰ ቃል ተናባቢ ሲሆን፦ በዚህ ጊዜ ሳድስ የነበረው መድረሻ ቀለሙ ወደ ግእዝ ይለወጣል።

ምሳሌ፦ መሰረት- መሰረተ ሕይወት፣ መሰረተ ዓለም

መንግሥት- መንግሥተ ሰማይ፣ መንግሥተ እግዚአብሔር ፣ መንግሥተ ዳዊት

ቤት - ቤተ መጽሐፍት፣ ቤተ እዚአብሔር፣ ቤተ አማኑኤል

ሊቅ - ሊቀ ካህናት፣ ሊቀ መላእክት፣ ሊቀ ጠበብት

ገብር -ገብረ አምላክ፣ ገብረ ኢየሱስ

ለ. በሣልስ የደረሰ ቃል ተናባቢ ሲሆን፡- በዚህ ጊዜ ሣልስ የነበረው መድረሻ ቀለሙ ወደ ኃምስ ይለወጣል።

ምሳሌ፡- ቀናዒ - ቀናዔ ቢጹ(በጓደኛው የሚቀና)

ብእሲ - ብእሴ እግዚአብሔር(የእግዚአብሔር ሰው)

ወሃቢ -ወሃቤ ሰላም(ሰላምን የሚሰጥ፣የሰላም ሰጭ)

ገባሪ - ገባሬ መንክራት(ድንቅ የሚሰራ)

ሐ. በራብዕ የደረሰ ቃል ተናባቢ ሲሆን፡- በዚህ ጊዜ ራብዕ የነበረው መድረሻ ቀለሙ ሳይለወጥ ራብዕ ይሆናል።

ምሳሌ፡- ዜና - ዜና አበው ፣ (የአባቶች ነገር)

ደመና -ደመና ሰማይ፣ (የሰማይ ደመና)

ሰረገላ -ሰረገላ እሳት፣ (የእሳት ሰረገላ)

መ. በኃምስ የደረሰ ቃል ተናባቢ ሲሆን፡- በዚህ ጊዜ ኃምስ የነበረው መድረሻ ቀለሙ ሳይለወጥ ኃምስ ይሆናል።

ምሳሌ፡- ዝማሬ - ዝማሬ ዳዊት፣ ዝማሬ መላእክት

ምናኔ - ምናኔ ዓለም

ውዳሴ -ውዳሴ ማርያም፣ ውዳሴ አምላክ

ሠ. በሳብዕ የደረሰ ቃል ተናባቢ ሲሆን፡- በዚህ ጊዜ ሳብዕ የነበረው መድረሻ ቀለሙ ሳይለወጥ ራሱ ሳብዕ ይሆናል።

ምሳሌ፡- መሰንቆ - መሰንቆ ዳዊት (የዳዊት መሰንቆ)

አእምሮ - አእምሮ መጻሕፍት(የመጻሕፍት እውቀት)

ተዋርዶ -ተዋርዶ ክብር

**ማስታወሻ**፡-፩ ከላይ ካየናቸው ተናባቢዎች የሚለይ ተናባቢ አለ። ይህ የተናባቢ ዓይነት ሲተረጎም ከላይ እንዳየነው «የ» በመጨመር ሳይሆን «እንደዚህ የሚባል» እየተባለ ነው።ይህ ተናባቢ የስያሜ ተናባቢ ይባላል።

ምሳሌ፡- መልአከ ገብርኤል -ገብርኤል የሚባል መልአክ

ሰማዕተ ጊዮርጊስ - ጊዮርጊስ የሚባል ሰማዕት

፪ ከላይ ካየናቸው ሥርዐተ ንባብ ሌላ በመጥበቅ እና በመላላት የቃላት ሥርዓተ ንባብ ይለያያል።

**ሀ. ላልቶ መነበብ**

በአብዛኛው የእነዚህ ቃላት መሰረታቸው ቀተለ ነው።እነዚህን ቃላት(ላልተው የሚነበቡትን) ያዝ ጠበቅ አድርጎ ማንበብ አይቻልም።

ምሳሌ፡- ተከለ፣ ወለደ፣ ሰከበ፣ መሐለ፣ መሰለ፣ ገብረ ፣ፈትሐ

**ለ. ጠብቆ መነበብ**

በአብዛኛው የእነዚህ ቃላት መሰረታቸው ቀደሰ ነው። ሶስት ዓይነት አጥብቆ የማንበብ ዘዴ አለ።

1) የተሰጠው ግስ የቀደሰ ቤት ሲሆን ምሳሌ፡- ጸውዐ፣ ሰብሐ፣ ጸለየ፣ ሐወጸ
2) ሁለት ደጊመ ቃላት ተደጋግመው ከመጡ አንዱ ተጎርዶ ሌላው ጠብቆ ይነበባል። ምሳሌ፡- ሐመመ=ሐመ፣ጠበበ=ጠበ፣ ነደደ=ነደ
3) በገዳፍያነ ዘመድ ቀለማት(ቀ፣ገ፣ከ፣ነ) የተነሳ የሚተብቁ አሉ።ምሳሌ፡-ሰጠቀ፣ ሰበከ፣አመነ፣ኀደግሙ

ምልማድ ፩

ሀ.የሚከተሉትን እውነት ወይም ሐሰት በሉ

1) ቅድመ መድረሻቸውተነስተው የሚነበቡ ቃላት ሁሉተነሽ ወይም ሰያፍ ይባላሉ።
2) በሳድስ ቀለም የሚደርስ ቃል ሁሉ ተጣይ ነው።
3) አእመረ ብሎ ተነሽ ካለ ቀተለት ብሎ ተጣይ ይላል።
4) በሰባቱም የሆሄ ስልቶች የሚነበበው ወዳቂ ንባብ ብቻ ነው።
5) ጠብቆ የሚነበብ ሁሉ የቀደሰ ቤት ላልቶ የሚነበብ ሁሉ የቀተለ ቤት ነው።

ለ.የሚከተሉትን ቃላት ተርጉሙ ሥርዓተ ንባባቸውንም በቅደም ተከተል አሳዩ።

1) ወዳግመ ይመጽእ አምላክነ በግርማ መንግሥቱ።
2) መጋቤ ብርሃናት ውእቱ ራጉኤል ሊቀመላእክተ።
3) ዝማሬ መላእክት ያስተፌስሕ አልባበ ቅዱሳን።
4) አልቦሙ እዝን ዘይሰምዑ ቦቱ ቃለ እግዚአብሔር።

## ፪.፫ የተጸውዖ ስሞች የንባብ ሕግጋት

የተጸውዖ ስሞች የሚባሉት የቦታ፣ የሰው፣ የሀገር ወዘተ መጠሪያ ስሞች ናቸው። በግእዝ ቋንቋ የተጸውዖ ስሞች የራሳቸው የሆነ ሥርዓተ ንባብ አላቸው። እንዲሁ በዘፈቀደ አይነበቡም። የተጸውዖ ስሞች በሶስቱ ንባባት ይነበባሉ። እነርሱም ወዳቂ፣ ተጣይ እና ሰያፍ

ናቸው። የተጸውዖ ስሞች ተነሽ ንባብ የላቸውም። ማንኛውም ከሳድስ ውጭ የጨረሰ ስመ ተጸውዖ ወድቆ የሚነበብ ሲሆን፤ በሳድስ የጨረሰ ደግሞ ተሰይፎ አሊያም ተጥሎ ይነበባል። በዚህ ክፍል በሳድስ የጨረሱ የተጸውዖ ስሞችን መለየት እንዴት እንደምንችል እንማራለን። በአጠቃላይ አንድ በሳድስ የጨረሰ የተጸውዖ ስም ሥርዓተ ንባብ ለማወቅ የሚከተለውን እንደመነሻ መውሰድ ይቻላል።

- ♣ ሦስት ቀለም ያለው ሆኖ በግእዝ ተነስቶ ድርድሩ ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ እና ሳብዕ የሆነ ስም ይሰይፋል።
  ምሳሌ፡- ከነዓን፣ ረዐብ፣ ዐረብ፣ ኢጋግ፣ አሳፍ፣ አዜብ፣ አቤል፣ አሞጽ፣ ወዘተ…
- ♣ በግእዝ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ የሆነ ስም ይሰየፋል።
  ምሳሌ፡- ዘሩባቤል፣ አማኑኤል፣ ወዘተ…
- ♣ በግእዝና በራብዕ ተነስቶ የመድረሻው አጠገብ ሣልስ የሆነ ስም አይሰየፍም።
  ምሳሌ፡- ናብሊስ፣ አቡቀለምሲስ፣ ወዘተ…
- ♣ በካዕብ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም ይሰየፋል።
  ምሳሌ፡- ሉቱኤል፣ ዱማቲዎስ፣ቡኤዝ፣ ወዘተ…
- ♣ በካዕብ ተነስቶ ድርድሩ ደካማ ቀለም ያለበት አይሰየፍም።
  ምሳሌ፡- ሱራፌል፣ ሩፋኤል፣ ኡራኤል፣ ወዘተ…
- ♣ በሣልስ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕና ሳብዕ የሆነ ስም ይሰየፋል።
  ምሳሌ፡- ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ ሲሞን፣ ቂርቆስ፣ ሲረዝምም ኢሳይያስ፣ ጢሞቲዎስ፣ ወዘተ…
- ♣ በሳልስ ተነስቶ ደካማ ሦስት ቀለም ሲደረደር፤ የመድረሻው አጠገብ ሣልስ፣ኃምስና ሳብዕ የሆነበት ስም አይሰየፍም።
  ምሳሌ፡- ጊዮርጊስ፣ ሚካኤል፣ ጲላጦስ፣ ሊባኖስ፣ ወዘተ…
- ♣ በራብዕ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ፣ ራብዕ፣ ኃምስና ሳብዕ የሆነ ስም ይሰየፋል።
  ምሳሌ፡- ሳሙኤል፣ ናባል፣ ሳቤቅ፣ ባሶር፣ ባሮክ፣ ወዘተ…
- ♣ በኃምስ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስና ሳብዕ የሆነ ስም ይሰየፋል።
  ምሳሌ፡- ሴኬም፣ ኤርምያስ፣ ቄርሎስ
- ♣ በኃምስ ተነስቶ ድርድሩ ሦስት ደካማ ቀለም የመድረሻው ኋላ ኃምስ መድረሻው ሳድስ የሆነ ስም አይሰየፍም።
  ምሳሌ፡- ኤልሳቤጥ፣ ኤልዛቤል፣ ኤልያቄም፣ ሄሮድስ፣ ወዘተ…
- ♣ በሳድስ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስና ሳብዕ የሆነ ስም ይሰየፋል።
  ምሳሌ፡- ብራኤል፣ ብሔሞት፣ ብልዮስ፣ ግዮን፣ ሲበዙም ከማሁ እለእስክንድሮስ፣ ወዘተ…
- ♣ በሳድስ ተነስቶ መካከሉ ሦስት ደካማ ቀለም ሲሆን አይሰየፍም።
  ምሳሌ፡- እስጢፋኖስ፣ እግዚአብሔር፣ ወዘተ…
- ♣ ፍፁም ሳድስ ሲሆን አይሰየፍም።
  ምሳሌ፡- እስክንድር፣ ግብፅ፣ ቅምር፣ ወዘተ…
- ♣ በሳብዕ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ፣ ኃምስና ሳብዕ የሆነ ስም ይሰየፋል።
  ምሳሌ፡- ቶማስ፣ ሮቤል፣ ሶፎር፣ ኮቦር፣ ወዘተ…
- ♣ በሳብዕ ተነስቶ የመድረሻው ኋላ ሣልስ ሲሆን አይሰየፍም።
  ምሳሌ፡- ሆለሆርኒስ
- ♣ ሁለት ቀለም የሆነ ስም ሁልጊዜም ተጥሎ ይነበባል እንጅ አይሰየፍም።
  ምሳሌ፡- ቡዝ፣ ካም፣ ኖኅ፣ አግ፣ ኖብ፣ ወዘተ…
- ♣ የመጨረሻው ቀለም ካእብ፣ ሣልስ፣ ራብዕ፣ ኃምስና ሳብዕ የሆነ ስም አይሰየፍም።
  ምሳሌ፡- ኢያሱ፣ ሱሲ፣ አቢሳ፣ ሙሴ፣ ጋይሶ፣ ወዘተ…

## ፪.፬ የሆሄያት ተጽእኖ

ቃላት ከላይ ያየናቸው የንባብ ሕግጋትን እንዲያፈርሱ የሚያደርጉ፤በሥርዓተ ንባብ ላይ ተጽእኖ የሚያመጡ ሆሄያት አሉ። እነርሱም ትራስ ቀለማት ይባላሉ። እነርሳቸውንም (ሰ፣ሂ፣ኒ፣ሃ) በዚህ ክፍል እናያቸዋለን።

**፩. ሰ** «ሰ» ከወዳቂ ቃላት ላይ ሲወድቅ(ከ«ዝ» ውጭ) ተነሽ ያደርጋቸዋል።ተጣይ(በሳድስ የሚጨርሱ) ቃላትን ግን አይለውጣቸውም (ወድቀው ይነበባሉ)።

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ምሳሌ፡-** | ወዳቂ | ተነሽ | | ወዳቂ | ተነሽ | | ተጣይ | ወዳቂ |
| | ዝንቱ | ዝንቱሰ | ........በካዕብ | እንበሌሁ | እንበሌሁሰ | .........በካዕብ | ዮም | ዮምሰ |
| | ከሣቲ | ከሣቲሰ | ..........በሣልስ | መከራ | መከራሰ | ...........በራብዕ | ምድር | ምድርሰ |

ይእዜ ይእዜሰ ..........በኃምስ ተዋሕዶ ተዋሕዶሰ ...........በሳብዕ

**«ሰ»** አንቀጽነት በሌላቸው (ግስ ባልሆኑ) ተነሽና ሰያፍ ቃላት ላይ ተደርቦ በወዳቂነት እንዲነበቡ ያደርጋል።

| ምሳሌ፡- ተነሽ | ወዳቂ | ተነሽ | ወዳቂ |
|---|---|---|---|
| አንተ | አንተሰ | ግብርከ | ግብርከሰ |
| አምላክነ | አምላክነሰ | ገብርኤል | ገብርኤልሰ |
| አማኑኤል | አማኑኤልሰ | ውእቱ | ውእቱሰ |

**፪ «ሂ»፣«ኒ»፣«ሃ»**

«ሂ» እና «ኒ» በስም መድረሻ ላይ እየገቡ ም፣ እንኳን፣ ደግሞ፣ ግን ተብለው ይፈታሉ።በተነሽ እና በሰያፍ ቃላት ላይ ሲወድቁ በወዳቂነት እንዲነበቡ ያደርጋሉ። ወዳቂ እና ተጣይን ግን አይለውጧቸውም።

ምሳሌ፡- ኵኑ ቅዱሳነ እስመ አነሂ ቅዱስ
አነ አሐውር ወአንተኒ ትልወኒ
አነ እሰክብ ወእኑየኒ ይትነሣእ
} ያወድቋቸዋል።

አ ድንግል መላእክትኒ ይሰግዱ ለኪ
ወይእዜኒ ነገሥት ለብዉ
ወአዕይንቲሁኒ ኀበ ነዳይ ያስተሐይጻ
ወሣህሉኒ ለትውልደ ትውልድ ለእለ ይፈርህዎ
} ያወድቋቸዋል(አይለውጧቸውም)።

«ሃ» ሁልጊዜ በስሞች ላይ እየወደቀች ወድቀው እንዲነበቡ ታደርጋለች።

**ምልማድ ፪**

**፩ የተሰመረባቸውን ቃላት ሥርዓተ ንባብ ለዩ**

ሀ, ሰላም ለስዕልኪ እንተ ሰዐላ በእዱ ሉቃስ ጠቢብ እምወንጌላውያን አሐዱ

ለ, ገሪማ ገሪምከኒ

ሐ, አነኑ ዐቃቢሁ ለአቤል

መ, ኀበ ሀለዉ ክልዔቱ ወሠለስቱ ግቡአን በስምየ ሀሎኩ አነ ማእከሌክሙ

ሠ, እመሰ ትፈቅድ ፍጹመ ትኩን ሑር ወሢጥ ኵሉ ዘብከ ሀብ ለነዳያን ወታጠሪ መዝገበ በሰማያትወንዓ ትልወኒ

ረ, አንተ ኩክህ ወዲበ ዛቲ ኩክህ አሐንጻ ለቤተክርስቲያን ወአናቅጸ ሲኦል ኢይኄይልዋ

ሰ, እለ ውስተ ሲኦል ፃዑ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ

ሸ, ጊዜ ተሰዓቱ ሰዓት የዐርጉ መላእክት ምግባሮ ለሰብእ

ቀ, ውድስት አንቲ በአፈ ነቢያት ወስብሕት በሐዋርያት

**፪ ትክክኛውን መልስ ምረጡ**

1, ወነጸረት ብእሲተ ሎጥ ድኅሬሃ ወኮነት ሐውልተ ፄው የተሰመረበት ቃል ሥርዓተ ንባብ

ሀ, ተነሽ ለ, ወዳቂ ሐ, ተጣይ መ, ሰያፍ

2, ከተሰመረባቸው ቃላት ውስጥ ተጣይ ንባብ የያዘው የቱ ነው

ሀ, በኀሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ሐ, ዘበጸጋሁ ተፈጥረ ኵሉ

ለ, ስብሐቲሁ ዘእም ኀቤሁ ወዉዳሴሁ እምዚኣሁ መ, ቅዳሴ እግዚእ

3, ንስሐሰ ትሬስዮ ለዘአበሰ ከመዘኢአበሰ ለዘማዊ ድንግለ የተሰመረበት ቃል ሥርዓተ ንባብ

ሀ, ወዳቂ ለ, ተነሽ ሐ, ሰያፍ መ, ተጣይ

4, ትክክል የሆነው የቱ ነው

ሀ, ኢትክልዕዎሙ ለህጻናት ይምጽኡ ኀቤየ በሚለው ህጻናት የሚለው ቃል ወዳቂ ነው፡፡

ለ, አርዮስ ሰጠጣ ለልብስየ

ሐ, ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ተነሽ ነው

መ, ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር በሚለው ዐ/ነገር ታበጽሕ የሚለው ቃል ተጣይ ነው

5, ንዑ ንረድ ወንክዐው ነገሮሙ ለከለዳውያን ከሚለው ዐ/ነገር ንረድ የሚለው ሥርዓተ ንባቡ

ሀ, ወዳቂ ለ, ተነሽ ሐ, ተጣይ መ, ሰያፍ

6, «ጳውሎስሰ» የሚለው ቃል ሥርዓተ ንባብ ሀ, ወዳቂ ለ, ተነሽ ሐ, ተጣይ መ, ሰያፍ

7, ከሚከተሉት ውስጥ ልዩ የሆነው ሀ, ሮቤል ለ, ቶማስ ሐ, ሄሮድስ መ, ገብርኤል
8, «ሰ» በትራስነት ቢገባበት ለውጥ የማያስከትለው በየትኛው ቃል ነው? ሀ, ንሕነ ለ, ደራሲ ሐ, ቅዳሴ መ, ትምህርት
9, ወድቆ የሚነበበው የትኛው ነው። ሀ, ሚካኤልሰ ለ, አንተሰ ሐ, ውእቱ መ, ከብረ

**፫ ,ከሚከተለው አጭር ምንባብ የተሰመረባቸውን ቃላት ሥርዓተ ንባብ ለዩ**

" አ ኣኃው ተዐቀቡ እምስካር እስመ <u>**ስካር**</u> ይዘሩ ልበ ወያደክም <u>**ሥጋ**</u> ወይሬስዮ ለብእሲ ይኩን <u>**ማኅደሮ ለሰይጣን**</u> ወያረስዖ ትሕርምታተ ዘእግዚአብሔር ወያተነትኖ ማዕከለ ሰብእ ወያመጽዕ <u>**ላዕሌሁ**</u> ኵሎ ነገረ ኃፍረት ወኃሣር ወዓዲ <u>**ይከውን ዕልወ**</u> ወይመርሖ ውስተ ቀትል ወይስሕቦ ውስተ ዝሙት ወዘይመስሎ <u>**ለዝንቱ**</u> ወያሐጕል ንዋዮ <u>**ወያረስዖ**</u> ጸሎተ ወኢያዜክሮ <u>**አምላኮ**</u> ወለብእሲ ስኩር ይሴሰል ይርኅቁ እምኔሁመላእክት ወዝከሉ ይረክቦ በዝ ዓለም

## ፪.፭ መጠይቃን ቃላት

የአንድን ሰው ማንነት፤ የነገርን ምንነት ፤ የጊዜን መቼነት፤ የቦታን የትነት፤ የቁጥርን ስንትነት ወዘተ ለመጠየቅ የምንጠቀምባቸው ቃላት መጠይቃን ቃላት ይባላሉ። የጥያቄ ጥያቄነት የሚታወቀው በመጠይቃን ቃላቱ ነው እንጅ በጥያቄ ምልክት አይደለም። እነዚህም መጠይቃን ቃላት የሚከተሉት ናቸው።

**፩, የሰውን ማንነት ለመጠየቅ** የምንጠቀማቸው «መኑ» እና«አይ» ናቸው። በዐ.ነገር ውስጥ«ማን» ተብለው ይተረጎማሉ። ፊደላትን እየደረቡ ትርጉማቸውን ይለውጣሉ። ምሳሌ:- ለመኑ---ለማን፣ በመኑ---በማን፣ ከመመኑ----እንደማን ወዘተ ።«መኑ»እና «አይ» ከአስሩ መራሕያን ጋር ሲያገለግሉ በብዙ ቁጥሮች «እለ» ን ከፊት እያስገቡ ነው። እለመኑ የሚለው «እነማን» ተብሎ ይፈታል።

| በነጠላዎቹ | በብዙዎቹ |
|---|---|
| መኑ አነ /አይ አነ | እለመኑ ንሕነ /እለአይ ንሕነ |
| መኑ አንተ /አይ አንተ | እለመኑ አንትሙ/እለአይ አንትሙ |
| መኑ አንቲ /አይ አንቲ | እለመኑ አንትን /እለአይ አንትን |
| መኑ ውእቱ /አይ ውእቱ | እለመኑ ውእቶሙ/እለአይ ውእቶሙ |
| መኑ ይእቲ /አይ ይእቲ | እለመኑ ውእቶን/እለአይ ውእቶን |

ምሳሌ:- መኑ/አይ ዘተሰቅለ በቀራንዮ
መኑ/አይ ዘሣረራ ለምድር
መኑ/አይ ዘነበበ ሐሰተ

**፪, የነገርን ምንነት ለመጠየቅ** የምንጠቀማቸው «ምንት» እና«አይ» ናቸው።በዐ.ነገር ውስጥ«ምን» «ምንድን» ተብለው ይተረጎማሉ። ፊደላትን እየደረቡ ትርጉማቸውን ይለውጣሉ።ምሳሌ:- ለምንት---ለምን፣ ምንተ---ምንን(ተሳቢ) ፣ ምንታት---ምኖች(በብዙ) ወዘተ ። ምንት በአስሩ መራሕያን ይዘረዘራል። አዘራዘሩም እንደሚከተለው ይሆናል።

| | |
|---|---|
| ምንቱ =ምኑ ......በውእቱ | ምንታ=ምኗ ......በይእቲ |
| ምንቶሙ=ምናቸው......በውእቶሙ | ምንቶን =ምናቸው...በውእቶን |
| ምንትከ =ምንህ ......በአንተ | ምንትኪ=ምንሽ ......በአንቲ |
| ምንትከሙ=ምናችሁ...በአንትሙ | ምንትክን=ምናችሁ...በአንትን |
| ምንትየ =ምኔ ......በአነ | ምንትነ=ምናችን ...በንሕነ |

ምሳሌ:- እግዚአብሔር ምንትነ ውእቱ ለነ
ክርስቶስ ምንታ ውእቱ ለማርያም

ማስታወሻ: «መ» በትራስነት እየገባ ተነስቶ እንዲነበብ ያደርገዋል።

ምሳሌ:- መኑመ ሰብእ ኢያአምሮ ለዝንቱ ወልድ። መኑመ ኢያአምር ምጽአቶ ለክርስቶስ።

ምልማድ ፫

ሀ, የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።መልሳችሁን በግእዝ ቋንቋ ጻፉ።

1. ለመኑ ተውህበ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ወለእለመኑ ተውህበ ዝንቱ መካን።
2. ለመኑ እለመኑ ተሰቅሉ ምስለ ክርስቶስ።
3. ለምንት ይደክም ሰብእ ኵሎ ጊዜያት።
4. አልአዛር ምንቶን ውእቱ ለማርያም ወለማረታ።
5. ዳዊት ምንቱ ውእቱ ለሰሎሞን።
6. አ ወልድየ ምንትከ ውእቱ ዘሐመከ።

7. ኤልሳቤጥ ምንትኪ ይእቲ ወለተ እምኪ።
8. በመኑ ተገብረ ዝንቱ ግብረ ኃጉል።
9. እለመኑ ውእቶሙ ዘልሣነ ግእዝ መምህራኒክሙ።

ለ, የሚከተሉትን ተርጉሙ።

1. እለመኑ ተዐሰሩ ወእለመኑ ተፈትሑ።
2. እለመኑ አንትሙ ዘታስተዋርዱ ክብረነ።
3. መኑ ፈጠሮ ለእጓለእመሕያው ወመኑ ሣረሮ ለሰማይ።
4. በምንት ይመጽእ ኤርምያስ በሰረገላኑ ወሚመ በእግር።
5. አ አንስት ምንከን ውእቱ ዝንቱ ወሬዛ።

**፫, የጊዜን መቼነት ለመጠየቅ** የምንጠቀማቸው «ማእዜ» እና«አይ» ናቸው።አንድ ድርጊት የተከናወነበትን ጊዜና ሰዐት ለመጠየቅ የምንጠቀምባቸው ቃላት ናቸው። ምሳሌ፡- ማእዜ ተሠገወ ወልደ እግዚአብሔር።

ማእዜ ውእቱ ዘተወለድከ እኁየ።

**፬, የቦታን የትነት ለመጠየቅ** የምንጠቀማቸው «አይቴ» እና«አይ» ናቸው።«የት»የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን ቦታን ለመጠየቅ ይጠቅማል። ምሳሌ፡- አይቴ ሖረ ወልድየ ወአይቴ ኀደረ። አይቴ ብሔራ ለጥበብወአይቴ ማኀደራ።

አይቴ አሐውር እምቅድመ ገጽከ። እምኀበ አይቴ ውእቱ መካኑ ዘተቀብረ ክርስቶስ።

**፭, ሁኔታን ለመጠየቅ** የምንጠቀመው «እፎ»ን ነው።ትርጉሙም እንዴት፣ ምንኛ፣ ምነው የሚል ፍቺ ያለው የንዑስ አገባብ ክፍል ነው። ለሰላምታ እና ለደህንነት መጠየቂያ ይሆናል። ከሌሎች ቀለማት ጋርም ሲጫፈር ሌላ ትርጉም ይኖረዋል።

ምሳሌ፡- በእፎ---ለምን፣ለምንድን ፤ እፎ እፎ---እንዴት እንዴት

እፎ ወጠንክሙ ትምህርተ ግእዝ።

እፎ የዐቢ ዕቡይ ርእሶ።

ማስታወሻ፡-«ኑ፣መ፣ኪ፣እንጋ፣ኢ» በቃሉ መድረሻ እየገቡ ግሡን ያጋንኑታል።

ከመዝኑ እንጋ አምኃ ይትአምኁ።

**፮, የቁጥርን ስንትነት ለመጠየቅ** የምንጠቀማቸው «እስፍንቱ» እና«ስፍን» ናቸው። ስፍን ለነጠላ ሲሆን እስፍንቱ ደግሞ ለብዙ ቁጥር ያገለግላሉ። በገቢርነት ለመናገር መድረሻውን ወደ ግእዝ ቀለም መለወጥ ነው።

ምሳሌ፡- ስፍነ ዘመነ ሀለውከ በዝንቱ መካን።

ስፍን ውእቱ መዋዕሊከ።

**፯, በግስ መድረሻ እየገቡ ለመጠየቅ** የምንጠቀማቸው «ኑ» እና«ሁ» ። በግሥ መድረሻ ላይ ገብተው ግሡን መጠይቃዊ ያደርጉታል። በዐ.ነገር ውስጥ «ን» ተብለው ይፈታሉ።

ምሳሌ፡- ሀሎኑ በዝ ሰማይ አምላከ እስራኤል አዶናይ።

አኮኑ ለእግዚአብሄር ትገኒ ነፍስየ።

በይነምንት ይዜኀር ባዕል ላዕለ ነዳይ። ኢይነዲሁ ዘብዕለ ወኢይብዕልሁ ዘነድየ።

**፰, ቦኑ** በዐ.ነገር ውስጥ «በውኑ» ተብሎ ይተረጎማል። በአብዛኛው «እፎ» ፣«በእፎ»፣«ለምንት» የሚባሉትን ቃላት አስቀድሞ ይነገራል።

ምሳሌ፡- በእፎ ያፈቅር ስብእ ዓለመ ቦኑ ይመስሎ ኢየኀልፍ።

ቦኑ በከንቱ ፈጠርኮ ለእጓለእመሕያው።

ምልማድ ፬

ሀ, ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በግእዝ ቋንቋ ጻፉ።

1. ማእዜ ይመጽእ ክርስቶስ ቀማእዜ ይከውን ኅልፈተ ዓለም።
2. እስከማእዜኑ እግዚኦ ትረስአኒ ለግሙራ።
3. አይ ዕለት ተሰቅለ ክርስቶስ ዐለተ ዓርብኑ ወሚመ ዕለተ ረቡዕ።
4. ማእዜ መጻእክሙ ኀበ ዝንቱ መካን ወማእዜ ተሐውሩ እምዝንቱ መካን።
5. እፎ መጻእከ ጳውሎስ ኀበ ዝንቱ መካን ኢተሐፍርኑ በዘገበርኮ።
